ሥ/ቤ ኖ ባሚመሩባ ው መርሆኖ

አዘ ኖ፡
ተሰ ትኦ
አለማባሁ ተ ት

ማው

ኽ

ባኮ ሑዊ መ ቢቨ

ክምል አትታ፡ ባ ፖትፔ ትቚፔ መርህ 1

መ ቢቨ

1.1. ባ ፖትፔ ትቚፔ ምትፔ 1

1.2. ባ ፖትፔ ትቚፔ ኽ ምኖ 4

1.2.1. ባ ኣኖ ለሰባዊ ትቚፔ 4

1.2.2. ውስኃዊ ትቚፔ 7

1.2.3. ተቋማዊ ትቚፔ 8

1.3. ባ ፖትፔ ትቚፔ ለምትየ 10

ባመወቨቨ ኅ ቨቄምኖ 11

1.4. ባ ፖትፔ ትቚፔ በኢ..ወ.ታ.ሪ መት ሥፔ፡- ጸአለም አቀም ዝቅተኾ

መመዘቖምኖ ጸአት ትታ ሀ ሮኖ ልምታ አትቚር 12

1.4.1. መ ቢቨ 12

1.4.2. ባሕ ኅ በቃ 14

ባመወቨቨ ኅ ቨቄምኖ 15

1.4.3. አስተ ተራዊ ትቚፔ 16

1.4.3.1. ኣኖ አ ታ ም ሰ ሠራተኣኖት ባማስተተሐር ሕትፔ 16

ባመወቨቨ ኅ ቨቄምኖ 18

1.4.3.2. ባበ ፔ ሕትፔ 19

ባመወቨቨ ኅ ቨቄምኖ 20

1.4.4. ባ ኣኖ ምልመለ ሹመፔ..... 20

ባመወቨቨ ኅ ቨቄምኖ 23

1.4.5. ባሥራ ዘመት ዋስፔ ጸሥራ መሰ በፔ ሥርዓፔ 24

ባመወቨቨ ኅ ቨቄምኖ 26

1.4.6. በቂ ክምቨ 26

ባመወቨቨ ኅ ቨቄ 27

1.4.7. ዝውውር ዕታ ፔ 27

ማኅ ቃለቨ ባመወቨቨ ኅ ቨቄምኖ 28

ክ*ል ሁለ፡- ባ ፖ*ፔ ተጎ*ቂ*ፔ ል*ኽ*ፔ መርህ 30

መ ቢ*

2.1. ባ ፖ*ፔ ተጎ*ቂ*ፔ 31

2.1.1. ባ ፖ*ፔ ተጎ*ቂ*ፔ ም*ት*ፔ 31

2.1.2. ባ ፖ*ፔ ተጎ*ቂ*ፔ ለም*?..... 33

2.1.3. ባ ፖ*ፔ ተጎ*ቂ*ፔ *ኽ ም*ኖ አ*ት*ት ኖ በጎ ቅላላው 34

ባመወ*ወ*ቨ ጎ*ቂ 36

2.1.4. ባ ፖ*ፔ ተጎ*ቂ*ፔ በኢ.ዋ.ታ.ሪ. 36

2.1.4.1. መ ቢ* 36

2.1.4.2. ባ*/ቤ ኖ ኣ ኖ ለሕ አው ው አካል ቨለባ ው ተጎ*ቂ*ፔ 37

2.1.4.3. ባወት ል ተጎ*ቂ*ፔ 39

2.1.4.4. ባ ኗስዞ ሊት ተጎ*ቂ*ፔ 39

ባመወ*ወ*ቨ ጎ*ቂ*ም*ኖ 42

2.2. ባ ፖ*ፔ ል*ኽ*ፔ 43

ባመወ*ወ*ቨ ጎ*ቂ*ም*ኖ 44

ዋቢ ኮ*ሑዐ*ኖ

ክፍል አንድ

የዳኝነት ነፃነት መርህ

መግቢያ

በዚህ ኮሑዎ መግቢያ እንደተመለከተው ፍ/ቤቶች ያላባቸውን ሕገመንግስታዊ ተልኮ ለማውጣት ሊመሩባቸው ከሚገባቸው መሰረታዊ መርሆች ውስጥ አንድ የዳኝነት ነፃነት ነው። የዳኝነት ነፃነት መርህ ተግባራዊ ለማታረ በቂ የህግ ማዕቀፍ(legal framework) መኖር አለመኖሩን እትሩም ስለመርሁ ተግባራዊ አፈፃፀም በቂ ግንዛቤ ለመጨበጥ የመርሁ ምንነት፣ ገፅታዎችና የመርሁ አስፈላጊነት በመጀመሪያ ግልፅ መደረግ አለባቸው። ከዚህም አንፃር የኢትዮጵያ ሥርዓት ለመፈተሽ የዳኝነት ነፃነትት በተመለከተ አለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ ዝቅተኛ መመዘኛዎችንና የሌሎች ሐገሮችን ልምድ ማየቱ ጠቃሚ ነው። የዚህ ባመ መሪቨ ክምል አላማም ቨሔው ነው።

ሰልጣኞች ይህን ክፍል ሲያጠ ቅቁ፡-

- የዳፖት ነፃነት ምንነት ያስረዳሉ።
- የዳኝነት ነፃነት ገፅታዎች ምን እትደሆኑ ይገልፃሉ።
- የዳኝነት ነፃነት አስፈላጊነት(ግብና ዓላማ) ጠንቅቀው ይገነዘባሉ።
- የዳኝነት ነፃነት አለም አቀፍ ዝቅተኛ መመዘኛዎች ምን እንደሆኑ አንድ በአንድ ይተነተናሉ።
- የዳኝነት ነፃነት ለማስፈንና ለማረጋገጥ ሌሎች ሐገሮች የዘረጉት ሥርዓት ምን እንደሚመስል በቂ ግንዛቤ የጨብጣሉ።
- በኢ.ኢ.ፌ.ድ.ሪ. ሥርዓተ መንግሥት የዳኝነት ነፃነትን ለማስፈንና ለማረጋገጥ ያለውን የህግ ማዕቀፍ ከሌሎች ሐገሮች ልምድ ጋር ያነፃፅራሉ።
- የዳኝነት ነፃነት መርህ ተግባራዊ አፈፃፀም በተመለከተ በቂ ገንዛቤ ይኖራቸዋል።

- የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ነፃ የሆነ የዳኝነት አካል የሚጫወተውን ወሣኝ ሚና ተረድተው በቁርጠኝነት ለተግባራዊነቱ ይነሳሳሉ፡፡ ይሰራሉ፡፡

1.1 የዳኝነት ነፃነት ምንነት

የዳኝነት ነፃነት መርህ በበርካታ ሊቃውንትና ዳኞች፣ ጠበቆች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የተነገረለትና የተፃፈበት ጉዳይ ነው፡፡ በበርካታ ሐገሮችም ህገመንግስታዊ እውቅናና ጥበቃ የተደረገለት መርህ ነው፡፡ ሆኖም ግን የዳኝነት ነፃነት ተለዋዋጭ ፅንሰ ሐሳብ በመሆኑ ስለዳኝነት ነፃነት መርህ ምንነት ወጥ የሆነ ትርጉም የለም፡፡ ፀሐፊዎች የዳኝነትን ነፃነትን በተለያየ መንገድ ለመግለፅ ሞክረዋል፡፡ ለምሳሌ እንደ **ኬ.ሮሲን** የዳኝነት ነፃነት ማለት፡

> *"The degree to which judges actually decided cases in accordance with their own determinations of the evidence, the law and justice, free from the coercion, blandishments, interference or threats from governmental authorities or private threats."*

በተመሳሳይ መልኩ **ፒኒ ጄ ዋይት** የዳኝነት ነፃነትን እንደሚከተለው ገልፆታል፡-

> *Judicial independence is the independence of judges in their judicial capacity from control by inappropriate external forces, pressures or threats.*

የዳኝነት ነፃነት ማለት ዳኞች ካለምንም ውጪ ጣልቃ ገብነት፣ ተፅእኖና ግፊት የቀረበላቸውን ጉዳይ ሕጉንና ማስረጃ ብቻ መሠረት በማድረግ ለመወሰን ያላቸውን ነፃነት እንደሆነ ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ትርጉሞች መረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን ከላይ የተጠቀሱት ትርጉሞች ሙሉ አይደሉም፡፡ ትርጉሞቹ የሚያተኩሩት በውሳኔ አሰጣጥ ወይም በፍርድ አሰጣጡ ሒደት ዳኛ ያለው ነፃነት ላይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የዳኝነት ነፃነት ባለቤት (subject of independence) ዳኞች መሆናችውን መረዳት ይቻላል፡፡ነገር ግን በዘመናዊ የዳኝነት ነፃነት ፅንሰ ሐሳብ መሰረት የዳኝነት

ነፃነት ባለቤት ዳኞች ብቻ ሳይሆኑ ፍ/ቤቶችን እንደ ተቋም የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር **ክርስቶፈር ላርኪን** የተባለ ፀሐፊ የዳኝነትን ነፃነት ሲገልጽ፡-

> *"Judicial independence refers to the existence of judges who are not manipulated for political gain, who are impartial toward the parties of a dispute and who form a political branch which has the power as an institution to regulate the legality of government behavior, enact neutral justice..."*

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የዳኝነት ነፃነት ባለቤት ዳኞችና ፍ/ቤቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ይህ በላርኪን የተሰጠው ትርጉም ሁሉ አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ትርጉሞች የበለጠ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ሌላው መታየት ያለበት ነጥብ ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ሲወስን ነጻ መሆን ያለበት ከማነው የሚለው ነው፡፡ ከላይ **በኬ ሮሲንና ከፒኒ ጄ ዋይት** ከተሰጡት የዳኝነት ነፃነት ትርጉሞች መገንዘብ እንደሚቻለው ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ሲወስን ነፃ መሆን ያለበት ከውጪ ማለትም ከመንግስትና ከግለሰቦች አለአግባብ ጣልቃ ገብነት፣ ተጽእኖና ግፊት ነው፡፡ ከዚህ አንጻርም ዘመናዊ የዳኝነት ነፃነት ጽንሰ ሐሳብ ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ሲወስን ከእነዚህ አካላት ነፃ መሆንን ብቻ የሚያጠቃልል ሳይሆን ከሕዝብ፣ ከሚዲያና ከፖለቲካ ድርጅት ነፃ መሆንን የሚያጠቃልል ነው፡፡

በተጨማሪም የዳኝነት ነፃነት ፅንሰ ሐሳብ ዘመናዊ አስተሳሰብ ዳኛ ቀረበለትን ጉዳይ ሲወስን ከውጪ ከየትም አቅጣጫ ከሚመጣ አለአግባብ ጣልቃ ገብነት፣ ተፅእኖና ግፊት ነፃ መሆን ብቻ ማለት ሳይሆን ከውስጥም ማለትም ከበላይ አለቆች፣ በላይኛው ፍ/ቤቶች እርከን ከሚገኙ ዳኞችና ከዳኛው ጋር አብረውት ከሚሠሩ ዳኞች ሊደርስበት ከሚችል አለአግባብ ጣልቃ ገብነት፣ ተጽእኖና ግፊት ነጻ መሆንን የሚጨምር ነው፡፡

በአጠቃላይ የዳኝነት ነፃነት ቀደም ሲል ይሰጠው የነበረው ትርጉምና በአሁኑ ዘመን ያለው ትርጉም አንድ አይደለም፡፡ ሐገሮችም ከሚከተሉት የህግ ሥርዓትና ሊያሳኩት ካሰቡት ግብ አኳያ ለዳኝነት ነፃነት የተለያዩ ትርጉሞች ሊሰጡት ይችላሉ፡፡ በአንድ ሐገርም በተለያዩ ጊዜያት የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- አሜሪካን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የዳኝነት ነጻነትም ይዘትም በየጊዜው አዳዲስ ሐሳቦች እየተጨመሩበት ሰፊ ትርጉም እየያዘ የመጣ ፅንስ ሐሳብ ነው፡፡ ሆኖም ግን መሰረታዊ ይዘቱ (essence) እንደያዘ ቆይቷል፡፡

1.2. የዳኝነት ነፃነት ገፅታዎች

የዳኝነት ነፃነት የተለያዩ ገፅታዎች (aspects) እንዳሉት ከላይ የዳኝነት ነፃነት ምንነት አስመልክቶ ከተሰጠው ማብራርያ መረዳት ይቻላል፡፡ ብዙ ፀሐፊዎች የዳኝነት ነፃነትን ገፅታ በሁለት ይከፍሉታል፡፡ እነሱም፡-

1. የዳኞች ግለሰባዊ ነፃነት
2. ተቋማዊ ነፃነት ናቸው፡፡

አንዳንድ ጸሐፊዎች ደግሞ የዳኝነት ነፃነትን ገጽታ በሦስት ይከፍሉታል፡፡ ለምሳሌ ፕሮፌሰር ሼሞን ሼትሪትን መጥቀስ ይችላል፡፡ እንደ ፕሮፌሰር ሼሞን ሼትሪት የዳኝነት ነፃነት ገፅታዎች፡-

1. የዳኞች ግለሰባዊ ነፃነት(Independence of Individual Judges)
2. ውስጣዊ ነፃነት (Internal Independence)
3. ተቋማዊ ነፃነት ናቸው፡፡ በዚህ ጽሁፍ የፕሮፌሰር ሼሞን ሼትሪትን አመዳደብ የምንከተል ይሆናል፡፡

1.2.1. የዳኞች ግለሰባዊ ነፃነት

እንደ ፕሮፌሰር ሼሞን ሼትሪትየዳኞች ግለሰባዊ ነፃነት ሁለት ንዑስ ገጽታዎች /ክፍሎች/ አሉት፡፡ እነሱም ውሳኔያዊ ነፃነት /decisional/ substantive/ /functional independence/ እና ግላዊ ነፃነት (personal Independence) ናቸው፡፡ ውሳኔያዊ ነፃነት ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን

ሲያከናውኑ ያላቸውን ነፃነት የሚመለከት ነው፡፡ እንደ ሼቲሪት ውሳኔያዊ ነፃነት ማለት፡

> *“Decisional independence means that in the making of judicial decisions and exercising other official duties, individual judges are subject to no other authority but the law.*

ዳኛ በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ከተከራካሪ ወገኖች በኩል ከሚቀርብ ክርክር፣ ፍሬ ነገር ማስረጃና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ በስተቀር ሌሎች ነገሮች ተፅኖ ሊያሳድሩበት አይገባም፡፡ በዚሁ መሰረት ውሳኔያዊ ነፃነት ውሳኔ አሰጣጡም ሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከማንኛውም መንግስት አካል፣ ባለሥልጣንና ግለሰብ አለአግባብ ጣልቃ ገብነት፣ ተጽእኖና ግፊት ነፃ መሆንን የሚጠየቅ ነው፡፡ ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ሲወስኑ ከእነዚህ አካላት ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መቀበል የለበትም፡፡

በተጨማሪም ውሳኔያዊ ነጻነት ከዳኛው የግል ፍላጎት፣ ስሜትና አድሎ ነፃ መሆንን የሚጠይቅ ነው፡፡ ዳኛ በሚቀርብለት ጉዳይ ላይ ምንም ፍላጎት የሌለው ገለልተኛ ውሳኔ ሰጪ መሆን አለበት፡፡ ሕዝቡ በፍ/ቤቶችና በዳኞች ላይ እምነት እንዲኖረው ዳኛ በሚወስነው ጉዳይና በፍርድ ሒደቱ ላይ ገለልተኛ ሆኖ መገኘት ብቻ ሳይሆን ገለልተኛ ሆኖ መታየትም አለበት፡፡ ዳኛ ገለልተኝነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ ከሚችሉ ተግባራትና ምግባር ሁሉ መቆጠብ ወይም ራሱን ማግለል ይጠበቅበታል፡፡

ውሳኔያዊ ነፃነት አስፈላጊነት የበለጠ የሚጎላው ከተከራካሪ ወገኖች ውስጥ አንድ የመንግስት አካል ወይም ጉዳይ የመንግስትን ጥቅም የሚነካ ወይም ከፖለቲካ ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን ነው፡፡ ዳኛ ተከራካሪ ወገን ማን ይሁን ማን በጉዳይ ላይ የሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የመንግስትን ጥቅም የሚጎዳ ይሁን አይሁን የፍ/ቤትን ገለልተኝነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ዳኝ በዳኝነት ሥራ ሂደት ውስጥ የእኩልነት መርህን ተግባራዊ በማድረግ የሕግ በላይነትን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ይህ ማንኛውም ዳኛ የዳኝነቱን ሥራ ሲያከናውን ሊመራበት የሚገባውና ሊተገብረው የሚገባ መርህ ነው፡፡ በተጨማሪም ዳኛ አንድን ጉዳይ ሲወስን

የሚፈራው ነገር መኖር የለበትም፡፡ የሕግ በላይነትን ከማረጋገጥና ከማስፈን ውጪ ሌላ የተለየ ጥቅም ለማራመድ የቆመ መሆን የለበትም፡፡ አንድ ፀሐፊ ይሔን በተመለከተ እንደሚከተለው በጥሩ ሁኔታ አስቀምጦታል፡፡

> *“The judge should decide cases solely based on the law and the facts that are applicable without regard to political or popular pressure,... fear of intimidation or special interests.”*

በሌላ በኩል ግላዊ ነፃነት ከዳኞች ሥራ ዘመን ዋስትና፣ ምልመላ፣ ሹመት፣ እድገት፣ ዝውውር፣ የዲሲፕሊን እርምጃ፣ ከሥራ ማሰናበት እና ከክፍያ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ሺሞን ሼትሪት ግላዊ ነጻነት እንደከሚከተለው ገልጸታል፡-

> *By personal independence of judges is to mean the enjoyment by individual judges of judicial terms of office and tenure free from the undue or improper influence and control of the political branches.*

የዳኞችን የሥራ ዘመን ከሕግ አስፈጻሚው ወይም ሕግ አውጪው ፍላጎት ላይ እንዲመሰረት ማድረግ ከዳኝነት ነጻነት መርህ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ በፍሬ ነገር፣ ማስረጃና አግባብነት ካለው ህግ ላይ ብቻ ተመስርቶ እንዲወስን ሁኔታዎች ሁሉ መመቻቸት አለባቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ የዳኞች ግላዊ ነፃነት ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ አንቱ ነው፡፡ ግላዊ ነጻነት የዳኞች የሥራ ዘመን ከሌሎች የመንግስት አካላት አለአግባብ ተጽእኖና ቁጥጥር ነፃ እንዲሆን የሚጠይቅ ነው፡፡

የዳኞች ምልመላ፣ ሹመት፣ ዕድገት፣ ዝውውር፣ የሥራ ዘመን፣ ዲሲፕሊን፣ ከሥራ ማሰናበት ሥርዓት እና ሌሎች ሁሉ የሕግ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ፡፡ የዳኝነት ነፃነት መርህ ይጠይቃል፡፡ አንድ ዕጩ ዳኛ እንዴት እንደሚመለመልና ለሹመት ሊያበቁ የሚችሉ መስፈርቶች ምን እንደሆኑ፣ ሿሚው አካል ማን እንደሆነ፣ የሹመቱ ዘመን ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ፣ ዳኛው ከተሾመ በኋላ ዕድገቱና ዝውውሩ በምን መስፈርት እንደሚከናወን የዲሲፕሊን እርምጃ ሥርዓት፣ ከሥራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ምክንያቶችንና ሌሎች ነጥቦችን የሚደነግግ ግልጽ ሕግ መኖር አለበት፡፡

1.2.2. ውስጣዊ ነፃነት

ውስጣዊ ነጻነት በቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት እያገኘ የመጣ የዳኝነት ነጻነት ሌላው ገጽታ ነው፡፡ ውስጣዊ ነጻነት ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ሲወስን ከበላይ አለቃ፣ ከበላይ ፍ/ቤቶች እርከን ከሚገኙ ዳኞችና አብረው ከሚሰሩት የሥራ ባልደረቦቹ አለአግባብ ተጽእኖና ግፊት ነጻ መሆንን የሚመለከት ነው፡፡

ውሳኔያዊ ነጻነትን እንውን ለማድረግ ውስጣዊ ነጻነትንን መረጋገጥ አለበት፡፡ ችሎትን በአግባቡ ለመምራት፣ ፍሬ ነገሮችን እና አግባብነት ያለውን ህግ ለይቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ዳኛው ከበላይ አለቆቹ፣ አብረውት ከሚሠሩ ዳኞች አለአግባብ ተፅእኖና ግፊት ነጻ መሆን አለበት፡፡ የነፃነቱ ሥፋት ግን የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ዳኛ ብቻ በሚሰየምበት ችሎት የዳኝነት ተግባሩ በችሎቱ ለተሰየመው ዳኛ የተተወ ነው፡፡ በተመሳሳይ እርከን ላይ የሚገኝ ማንኛውም ዳኛ ወይም የበላይ አለቃ ዳኛው የያዘውን ጉዳይ አስመልክቶ መመሪያ ወይም ተጽኖ እንዲያሳድር መፍቀድ የለበትም፡፡ የዳኛው የሥራ ባልደረቦችና የበላይ አለቃ ዳኛው በተወሰነ መንገድ ጉዳይ እንዲወስን ማግባባት የለባቸውም፡፡ በስነ ስርዓት ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ብይኖች ወይም ትእዛዞች ወይም ውሳኔዎች በችሎቱ የተሰየመው ዳኛ መሆን አለባቸው፡፡

ከአንድ ዳኛ በላይ በሚሰየመበት ችሎት እያንዳንዱ ዳኛ ሰብሳቢም ይሁን የግራ ወይም የቀኝ ዳኛ በሚቀርበው ጉዳይ የራሱን አቋም የማራማድ ነፃነት አለው፡፡ በውይይት ጊዜም ሆነ በውሳኔ አሰጣጡ ሂደት እያንዳንዱ ዳኛ ፍሬ ነገሮችን አግባብነት ያለውን ሕግ በተረዳው መንገድ ያለውን ሐሳብ የማንፀባረቅና በአብላጫው ውሳኔ ሐሳብም ካልተስማማ የሐሳብ ልዩነቱን የማስፈር ነጻነት ሊኖረው ይገባል፡፡

በተጨማሪም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች የሚሰየምበት ችሎት ዳኞች ከአለቆቻቸውና ከበላዮቻቸው አለአግባብ ተጽእኖ እና ቁጥጥር ነጻ መሆን አለባቸው፡፡ የፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንቶች፣ ሰብሳቢ ዳኞችና በላይኛው ፍ/ቤት እርከን የሚገኙ ዳኞች ሌሎች ዳኞች አንድን ጉዳይ ራሳቸው በሚፈለጉት መንገድ እንዲወስኑ ተጽእኖ ማድረግ የለባቸውም፡፡

በመጨረሻም በዳኞች ላይ የሚደረግ አስተዳደራዊ ቁጥጥር፣ የጉዳዮች አያያዝ የሚመለከቱ አስተዳደራዊ መመሪያዎች ውስጣዊ የዳኝነት ነፃነት ጋር የማይጋጩ መሆናቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

1.2.3. ተቋማዊ ነፃነት

የመንግስት ሥልጣንን በሦስት ማለትም ሕግ አውጪ፣ ህግ አስፈጻሚና ህግ ተርጓሚ ብሎ መከፋፈል የተለመደ ነው፡፡ ፍ/ቤቶች ህግ ተርጓሚ አካል ናቸው፡፡ የፍ/ቤቶች ተቋማዊ ነፃነትም ከዚሁ የመንግስት ሥልጣን ክፍፍል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ሙሑር ተቋማዊ ነፃነትን እንደሚከተለው በጥሩ ሁኔታ ገልጾታል፡-

> *Institutional independence of the judiciary means that the judiciary is not subject to pressure from either the executive or legislature and is not subordinate to either of them particularly in the area of administration of courts.*

ከዚህ አገላለፅ እንደምንረዳው ተቋማዊ ነፃነት ፍ/ቤትን እንደ ሦስተኛ የመንግስት አካል መቋቋምና መኖርን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ከሕግ አውጪና ከሕግ አስፈጻሚው ተፅእኖ በተለይም ፍ/ቤትን ማስተዳደር በተመለከተ ነፃ መሆኑን የሚጠይቅ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ተቋማዊ ነፃነት ፍ/ቤት እንደ ተቋም ከሕግ አውጪውና ከሕግ አስፈጻሚው አካል ተፅእኖ ነፃ ሆኖ የራሱን የውስጥ ጉዳይ ለመወሰን ያለውን ነፃነት የሚመለከት ነው፡፡

የፍ/ቤት የማስተዳደር ነፃነትም ሁሉት አብይ ክፍሎች አሉት፡፡ እነሱም ዳኞችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞን የማስተዳደር ነፃነትና የፋይናንስ ወይም የበጀት ነፃነት ናቸው፡፡ ዳኞችን የማስተዳደር ነፃነት የዳኞች ምልመላ፣ ሹመት፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ዲሲፕሊን፣ ከሥራ ማሰናበት፣ ደሞዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችና እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን መቅጠርና ማሰናበት በተመለከተ ፍ/ቤት አንድ ተቋም ሊኖረው የሚችለውን ነፃነት የሚመለከት ነው፡፡ የፋይናንስ ወይም በጀት አስተዳደር ነፃነት ደግሞ ፍ/ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን በጀት መጠን ግምት አዘጋጅተው ለሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ

ማቅረብና በጀቱም ከፀደቀ በኋላ ከሥራ አስፈጻሚው አካል ጣልቃ ገብነት ውጪ በጀቱን የማስተዳደር ነፃነትን የሚያጠቃልል ነው።

ከፍ/ቤቶች ተቋማዊ ነፃነት ጋር የሚነሳው ጥያቄ ፍ/ቤቶችን ማን ያስተዳድር የሚለው ነው። የፍ/ቤቶች የማስተዳደር ኃላፊነትን በተመለከተ የተለያዩ ሞዴሎች አሉ። እንደ ፕሮፌሰር ሼሞን ሼቲሪት አራት አይነት የፍ/ቤት አስተዳደር ሞዴሎች አሉ።

አንደኛው the exclusive judicial responsibility model የሚባለው ነው። በዚህ ሞዴል ፍ/ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ለፍ/ቤት የተተው ነው። ይህ ሞዴል ሁለት ንዑስ ሞዴሎች አሉት። አንደኛው individual ሞዴል ሲሆን በዚህ ንዑስ ሞዴል ፍ/ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ለአንድ ዳኛ የተተወ ነው። ለምሳሌ ኒዮርክ ሰቴት።ሁለተኛው collective ሞዴል ሲሆን በዚህ ንዑስ ሞዴል ፍ/ቤት የማስተዳደር ኃላፊነት ከፍ/ቤት ተውጣቶ ለተቋቋመ አካል የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ የአሜሪካን ፌደራል ፍ/ቤት፣ ጣሊያንና ፖርቱጋልን መጥቀስ ይቻላል።

ሁለተኛው the exclusive executive responsibility model የሚባለው ነው። ይህ ሞዴል የአንደኛው ተቃራኒ ነው። በዚህ ሁለተኛው ሞዴል ፍ/ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ለሕግ አስፈጻሚው አካል ነው። ለምሳሌ ኖርዋይና ኦስትሪያን መጥቀስ ይቻላል።

ሦስተኛው ሞዴል a shared executive judicial model የሚባለው ነው። በዚህ ሞዴል መሰረት ፍ/ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት በሕግ አስፈጻሚውና በፍ/ቤት የተከፋፈለ ነው። በዚህ ሞዴል መሰረት የማስተዳደሩ ኃላፊነት ክፍፍል በጎንዮሽ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ- ጀርመንና ካናዳ የላይኛዎቹን ፍ/ቤት የማስተዳደር ኃላፊነት የፍ/ቤቶች ሲሆን የበታችኞቹን ፍ/ቤቶች የማስተዳደር ኃላፊነት ደግሞ የሕግ አስፈጻሚው ነው።

አራተኛው ሞዴል a multi-branch responsibility model የሚባለው ሲሆን በዚህ ሞዴል መሰረት ፍ/ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት ከፍ/ቤትና ከሌሎች ከሦስቱም የመንግስት አካላት ማለትም ከሕግ አውጪ ወይም/እና ሕግ አስፈጻሚና እንዲሁም ከሌላ አካል ለምሳሌ

ከጠበቆች ማህበር ወይም ከሌሎች ሕብረተሰብ ክፍል የተወከሉ ሰዎች ለተውጣጣ አካል የተሰጠ ነው፡፡ ይህ አካል ቦርድ፣ኮሚሽን፣ ኮንፍረንስ፣ የዳኞች ጉባኤ ተብሎ በተለያየ ስም ይጠራል፡፡ ለምሳሌ፡- ከላቲን አሜሪካ ሀገሮች አርጀቲና ብራዚል ከምዕራብ አውሮፓ ደግሞ ስፔንና ጣሊያንን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በምዕራብ አውሮፓ ሐገሮች የዳኞች ጉባኤ ሕግ አስፈጻሚው በፍ/ቤቶች ላይ ያለውን ሥልጣን ለመገደብ የተቋቋመ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የዳኞች ሹመት፣ ዕድገትን ሥልጣን ከሕግ አስፈጻሚው ውጪ በማድረግ ራሱን ለቻለ ተቋም እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ሐገሮች የራሳቸው ልዩ ሁኔታ ያላቸውን የሕግ ስርዓትና ታሪክ ላይ በመመስረት ከላይ የተጠቀሱትን አንዱን ወይም ሁለቱን በማጣመር ወይም ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ሞዴሎችን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን የሞዴሎቹ ምርጫ ፍ/ቤቶች ሊኖራቸው በሚችለው ነጻነት ላይ የራሱን አሉታዊ ወይም አውንታዊ ተጽኖ ሊኖረው ይችላል፡፡

በተጨማሪም የዳኝነት ተቋማዊ ነፃነትን ለመጠበቅ ሌሎች ሊተገበሩ የሚገባቸው መሰረታዊ መርሆች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከመደበኛ ፍ/ቤት ውጪ ጊዜያዊ ፍ/ቤቶችን ማቋቋምን የሚከለክል መርህ (the principle against ad hoc courts) እና ከውሳኔ በኋላ ያለ የዳኝነት ነፃነት መርህ (the principle of post-decisional independence) ሊጠቅሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከውሳኔ በኋላ ያለ የዳኝነት ነፃነት መርህ በሶስቱም የመንግስት አካላት መካከል ያለ የሥልጣን ክፍፍልን መሰረት በማድረግ የሕግ አስፈፃሚ አካል የፍርድ ቤት ውሳኔን የመፈፀም ግዴታና በፍርድ አፈፃፀም ሒደት ላይ ምንም አይነት መሰናክል እንዳይፈጥር ግዴታ የሚጥል መርህ ነው፡፡

1.3. የዳኝነት ነፃነት ለምን?

ነጻ የሆነ ፍ/ቤት የሕግ በላይነት መሰረታዊ ገፅታና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖር ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የዲሞክራሳያዊ ሥርዓት ዋነኛው ባሕሪ ደግሞ የሰብአዊ መብቶች መከበርና መረጋገጥ ነው፡፡ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በሕገ-መንግስት ወይም በሌላ ሕግ መደንገጋቸው ብቻ በራሱ ለመብቶች መረጋገጥ ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ እነዚህ መብቶች ዕውን ይሆኑ ዘንድ ነፃ ፍ/ቤት መኖር አለበት፡፡ ነፃነት የሌለው ፍ/ቤት የሰዎችን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች እንዲረጋገጥ ሊያደርግ አይችልም፡፡

በዜጎችና በመንግስት እንዲሁም በሰዎች መካከል ባሉ ግንኙነት ሳቢያ የሚነሱ የፍትሐብሔር ወይም ወንጀል ክርክሮችን ገለልተኛና ነፃ ሆኖ እልባት ሊሰጥ የሚችል ፍ/ቤት በሌለበት የሕግ በላይነት ሊረጋገጥ አይችልም። የሕግ በላይነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና መልካም አስተዳደር እውን ሊሆኑ አይችሉም። ሰላምና ዘለቄታዊነት ያለው ልማትም ዋስትና አይኖረውም። ይሔን **ስቴፈን ጂ. ብሌየር**፡

> *Judicial independence is a means toward a strong judicial institution. Strong judicial institution is a means toward securing the basic goals of people: human liberty and a reasonable level of prosperity.*

በማለት በትክክል አስቀምጠታል።

የዳኝነት ነፃነት ለኢንቨስትመንትና ለኢኮኖሚ እድገት መሰረት ነው። ሕዝቡና ባለሐብቱ በፍ/ቤቶችና በዳኞች ላይ እምነት እንዲኖረው በአንድ ሀገር ውስጥ የዳኝነት ነፃነት መስፈንና መረጋገጥ ወሳኝ ነው። ስለዚህ ሰለዳኝነት ነፃነት አስፈላጊነት ላይ ምንም ክርክር የለም። ጥያቄው ያለው የዳኝነት ነፃነት ስፋትና (extent) እና ተግባራዊ አፈጻጸሙ ላይ ነው።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የዳኝነት ነፃነት መሰረታዊ ዓላማ ምንድነው?
2. በውሳኔያዊ ነጻነትና ግላዊ ነፃነት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?
3. የዳኞችን የሥራ ዘመን እንዴት ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል?
4. በውሳኔያዊ ነፃነትና ውስጣዊ ነፃነት መካከል ያለው ተመሳሳይነትና ልዩነት ምንድንነው?
5. የተቋማዊ ነፃነት ዋና አላማው ምንድንነው?
6. በተቋማዊ ነፃነትና በሌሎች የዳኝነት ነፃነት ግዕታዎች መካከል ያለው ግንኙነት እንዴት ይገለፃል?

7. ፍ/ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት በተመለከተ የተለያዩ ሞዴሎች እንዳሉ ከላይ ተመልክቷል። የእንያንዳንዱ ሞዴል ጠንካራን ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው? አንድ በአንድ ውይይት ይደረግበት።

1.4. የዳኝነት ነፃነት መርህ በኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት፡- ከአለም አቀፍ ዝቅተኛ መመዘኛዎች ከአንዳንድ ሐገሮች ልምድ አንጻር

1.4.1 መግቢያ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዳኝነት ነጻነት በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነትና ትኩረት ያገኘ መርህ ነው። ስለአስፈላጊነቱ አለም አቀፍ መግባባት (global consensus) መኖሩን የተለያዩ አለም አቀፍ፣ ሀገራዊና ብሔራዊ የሕግ ሰነዶችን ማየቱ በቂ ነው።

በሌላ በኩል በሀገሮች መካከል ባለው የፖለቲካ፣ የሕግና የኢኮኖሚ ልዩነቶች የመርሁ ይዘትና ተግባራዊ አፈጻጸም ደረጃ ይለያያል። የፍ/ቤቶች ነፃነት ደረጃና ስፋት ከሀገር ሀገር ይለያያል። የዳኝነት ነፃነትን ለማረጋገጥ ሀገሮች የሚከተሉት ስልት እንዲሁ የተለያየ ነው። ይህ ማለት ግን በአለም አቀፍ ደረጃ ይብዛም ይነስም የጋራ መግባባት የተደረሰባቸው የዳኝነት ነፃነት መሰረታዊ መርሆችና መመዘኛዎች የሉም ማለት አይደለም። የተባበሩት መንግስታት የፍ/ቤት ነፃነት መርሆች ረቂቅ (The United Nation's Draft Principles on the Independence of the Judiciary((1981) በመግቢያው ውስጥ ይሄን ፡-

> *"Notwithstanding the diversities of political systems and legal mechanism in different countries there is a basic and substantial consensus on the principles and minimum standards relating to the independence of justice in the constitutions and legal systems of the world".* በማለት ገልጸታል።

በዚህ አገላለጽ መሰረት በሀገሮች መካከል የፖለቲካና የሕግ ሥርዓት ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ስለ ዳኝነት ነፃነት መርህና ዝቅተኛ መመዘኛዎች መሰረታዊ የሆነ መግባባት አለ፡፡ እነዚህ የዳኝነት ነጻነት መሰረታዊ መርሆችና መመዘኛዎች በሚከተሉት አለም አቀፋዊ ይዘት ባላቸው ሰነዶች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡

1. የተባበሩት መንግስታት የፍ/ቤት ነጻነት መርሆች ረቂቅ (The United Nations Draft Principles on the Independence of the Judiciary) (1981)
2. የአለም አቀፍ ጠበቆች ማህበር የዳኝነት ነፃነት ዝቅተኛ መመዘኛዎች (The International Bar Association and Minimum Standards of Judicial Independence) (1982) ("New Delhi Standards")
3. የሞንቴሪያል ጀስቲስ ነፃነት ሁለ አቀፍ መግለጫ (The Montreal Universal Declaration on the Independence of Justice) (1983) ("Universal Declaration")
4. የተባበሩት መንግስታት የፍ/ቤት ነፃነት መሰረታዊ መርሆች (The United Nations Basic Principles on the Independence of the Judiciary)
5. የፍ/ቤት ነፃነትና ገለልተኝነት ሁለ አቀፍ መግለጫ ረቂቅ (Draft Universal Declaration on the Independence and Impartiality of the Judiciary) (1989)

የዳኝነት ነፃነት መስፈኑን ለማረጋገጥ የሚረዱ መስፈርቶች በእነዚህ ሰነዶች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሰነዶች የአስገዳጅነት ባህሪ ባይኖራቸውም የዳኝነትን ነፃነትን ለማስፈን ሊወስዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ወይም ሀገሮች ሊከተሉት የሚገባቸው ሥልቶችን የሚጠቁሙ በመሆናቸው ጠቀሚታቸው የጎላ ነው፡፡ በተጨማሪም የፍ/ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም እየተገበሩ ያሉ ሀገሮች የማሻሻያ ፕሮግራማቸውን ውጤታማነት ለመመዘን መስፈርቶች እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

በዚህ ጽሁፍም በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሥርዓተ መንግስት የዳኝነት ነጻነት መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰዱት ወይም እየተወሰዱ ያሉት እርምጃዎች ምን እንደሚመስሉ ትክክለኛውን ግንዛቤ ለመጨበጥ ከላይ በተጠቀሱት ሰነዶች ውስጥ የተቀመጡ መስፈርቶች ላይ የምንመሰረት ይሆናል፡፡

በእነዚህ ሰነዶች ውስጥ የተካተቱት አለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት ዝቅተኛ መመዘኛዎች የሥራ ዋስትና፣ በቂ ክፍያ እና ሕገመንግስታዊ ጥበቃ፣ የፍትሐብሔር ኢሙኒቲ፣ የውሳኔ አሰጣጥና ሂደት ከበላይ አለቆች ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን፣ የፍርድ ቤትን ውሳኔ በማስፈፀም በኩል የሕግ አስፈጻሚ እገዛ፣ ወደኋላ ተመልሶ የሚሰራ ሕግ አለመኖር፣ ግልጽ የሆነ የሥነ ምግባር ደንብ፣ አስተዳደራዊ ነጻነት፣ ዝውውር፣ ግልጽና ተጨባጭ የእድገት መመዘኛዎች እና ሌሎችም ይገኙበታል። ሆኖም ግን ሁሉንም መመዘኛዎች በዚህ ጽሑፍ ማቅረብ ስለማይቻል በሀገራችን የዳኝነት ነፃነትን ከማስፈን አኳያ የበለጠ አግባብነት ሊኖራቸው የሚችሉትን የሕግ ዋስትና፣ አስተዳደራዊ ነፃነት፣ የዳኞች ምልመላና አሿሿም፣ የሥራ ዘመን ዋስትና፣ በቂ ክፍያ፣ የዲሲፕሊንና ከስራ ማሰናበት ሥርዓት ብቻ የምንመለከት ይሆናል።

1.4.2. የሕግ ዋስትና

የዳኝነት ነፃነት ለማስፈን በመጀመሪያ መወሰድ ያለበት እርምጃ ለዳኝነት ነጻነት የሕግ ጥበቃ ማድረግ ነው። የተባበሩት መንግስታት የፍ/ቤት ነጻነት መሰረታዊ መርሆች ሀገሮች የዳኝነት ነፃነትን ለማስፈን ለዳኝነት ነጻነት ሕጋዊ ጥበቃ ማድረግ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህም በሰነዱ አንቀጽ 1 ሥር እንደሚከተለው ተቀምጧል፡

> *The independence of the judiciary should be guaranteed by state and enshrined in the Constitution and the law of the country.*

በዚህ አገላለጽ መሰረት የዳኝነት ነፃነት በመንግስት ዋስትና ሊኖረው ይገባል። የዳኝነት ነፃነት መርህም በሀገሪቱ ሕገመንግስት ወይም በሀገሪቱ ሕግ ውስጥም ሊካተት ይገባል።

ብዙዎቹ ሀገሮች ለዳኝነት ነፃነት መርህ ሕገመንግስታዊ እውቅናና ጥበቃ አድረገዋል።፤ በዚሁ መሰረት የዳኞች የሥራ ዘመን ዋስትና፣ ሹመት፣ ከሥራ መሰናበት፣ ደሞዝና ሌሎች ጉዳዮች በሕገ መንግስታቸው ውስጥ እንዲካተቱ አድረገዋል። ለዚህም የአውስትራሊያ፣ ብራዚል፣ ዩጋንዳ፣ ፈረንሳይ፣ ጀመርንና የቤልጀም ሕገ-መንግስት ለምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። አንዳንድ ሐገሮች ደግሞ ወደ

ዝርዝር ሳይገቡ የዳኝነት ነፃነት መከበሩን ብቻ ይገልጻለ፡፡ ይህ አይነት ጥበቃ በሌላ ሕግ መደገፍን ይጠይቃል፡፡

በአጠቃላይ የዳኝነት ነጻነትን ለማስፈን የዳኝነት ነጻነት ገፅታዎች ሕጋዊ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ እነዚህ የዳኝነት ነጻነት ገፅታዎች ቀደም ሲል በተጠቀሱ አለም አቀፍ ሰነዶች እውቅና ተሰቷቸዋል፡፡ ለምሳሌ ውሳኔያዊ ነፃነትን በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት የፍ/ቤት ነፃነት መሰረታዊ መርሆች እንደሚከተለው አስቀምጠታል፡፡

> *The Judiciary shall decide matters before them impartially on the basis of facts and in accordance with the law, with out any restrictions, improper influences, inducements, pressures, threats of interferences, direct or indirect form any quarter or for any reason..*

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ዳኞች የቀረበላቸውን ጉዳይ ሲወስኑ ገለልተኛ በመሆን ካለምንም ውስንነት፣ አለአግባብ ተፅእኖ፣ ማስፈራራት፣ ጫናና ጣልቃ ገብነት በቀረበላቸው ፍሬ ነገርና ማስረጃ ብቻ ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው የዳኝነት ነፃነት መርህ አጥብቆ ይጠይቃል፡፡ በዳኝነት ነፃነት መርህ ውስጥ ውሳኔያዊ ነፃነት ቁልፍ ቦታ አለው፡፡ *Decisional independence is sine qua of the judicial function.* ካለውሳኔያዊ ነፃነት የዳኝነት ነፃነት መርህ ትርጉም አልባ ነው፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኢ.. ፌ.ድ.ሪ ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓት ለዳኝነት ነጻነት ሁሉም ገጽታዎች ሕጋዊ ጥበቃ ተደርጓል? ተደርጓል የሚባል ከሆነ እያንዳንዱን የዳኝነት ነፃነት ገጽታዎችን ለማጠናከር በሕግመንግስቱ የተወሰዱ እርምጃዎች ምን ምን እንደሆኑ አንድ በአንድ ውይይት ይደረግበት፡፡

2. የዳኝነት ነፃነትን ሕጋዊ ጥበቃ በማድረግ አኳያ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግሥትና ከክልል መንግስታት ህገመንግስት መካከል ያለው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል?
3. የዳኝነትን ነጻነት መርህ ማክበርና ማስከበር የማን ኃላፊነት ነው?

1.4.3. አስተዳደራዊ ነጻነት

አስተዳደራዊ ነጻነት ፍ/ቤት እንደ ተቋም ዳኞችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን እንዲሁም በጀትን በማስተዳደር ረገድ ያለውን ነጻነት በዋነኝነት እንደሚመለከተ ቀደም ሲል ተመልክቷል፡፡

1.4.3.1. ዳኞችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የማስተዳደር ነጻነት

እንደ አለም አቀፍ የዳኝነት ነጻነት ዝቅተኛ መመዘኛዎች ፍ/ቤት የማስተዳደር ዋናው ኃላፊነት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ጨምሮ ለፍ/ቤት ወይም ከፍ/ቤትና ከሌሎች አካላቶች ለተውጣጣ አካል መስጠት አለበት፡፡ በዚህ አካል ውስጥ ከፍ/ቤት የሚወከለ ሰዎች አብላጫውን ቁጥር መያዝ አለባቸው፡፡ በዚህ መመዘኛ መሰረት የዳኞች ምልመላ፣ ሹመት፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ዲሲፕሊን፣ ከሥራ ማሰናበት እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን መቅጠርና ከሥራ መሰናበት ከሕግ አስፈጻሚው አካል ውጪ መሆን አለበት፡፡

በሌላ በኩል የቆየ የዲሞክራሲ ታሪክና ልምድ ባላቸው ሐገሮች የዳኞች ሹመትና ዕድገት ከፍ/ቤት ውጪ በሆነ አካል እንዲከናወን መሆኑ ከዳኝነት ነፃነት መርህ ጋር እንደማይጋጭ በአለም አቀፍ ጠበቆች ማህበር ዝቅተኛ የዳኝነት ነፃነት መመዘኛ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ግን የዲሞክራሲ ባህል ባልዳበረባቸው ሐገሮች ሌሎች የመንግስት አካላቶች በፍትህ አስተዳደር ውስጥ አይሳተፍም ማለት አይደለም፡፡ በፍትህ አስተዳደር ውስጥ የመንግስት አካላትን ተሳትፎ ማስወገድ አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን የዳኝነት ነፃነትን ለመጠበቅ የፍ/ቤትን የውስጥ ጉዳይ በተመለከተ የሕግ አስፈጻሚው ወይም የሕግ አውጪው አካል ተሳትፎ የመንግስት ስርዓቱ የግድ በሚላቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ የተገደበ መሆን አለበት፡፡ ለዚህም

የዳኞችን ሹመትና ከሥራ ማሰናበት እንዲሁም በጀትን ማፅደቅ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ፍ/ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት በተመለከተ የተለያዩ ሞዴሎች እንደሉና የሐገሮችም ልምድ የተለያየ መሆኑን ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ከተገለጹት ሞዴሎች ውስጥ a multi-branch responsibility ሞዴል ተብሎ የሚጠራው በብዙ ሐገሮች ተቀባይነት እያገኘ የመጣና በአለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት ዝቅተኛ መመዘኛ ሰነዶችም የተገለፀ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው a multi-branch responsibility model ፍ/ቤት የማስተዳደር ኃላፊነት ለፍ/ቤት ብቻ ወይም ለሕግ አስፈጻሚው ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ከፍ/ቤትና ከመንግስት አካላት እንዲሁም እንደ ሁኔታው ከሌላ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ሰዎች በተቋቋመ አካል የተሰጠ ነው፡፡ እንደአለም አቀፍ ዝቅተኛ መስፈርት መሰረት በዚህ አካል ውስጥ ከፍ/ቤት የሚወከሉ ሰዎች አብላጫውን ቁጥር መያዝ አለባቸው፡፡

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገመንግሥት የፍ/ቤቶችን ተቋማዊ ነፃነትን እውን ለማድረግ ፍ/ቤቶች የውስጥ ጉዳያቸውን በመወሰን ረገድ ያላቸውን ነጻነት ለማረጋገጥ በተለይም የዳኞችን ምልመላ፣ ዝውውር፣ የዲሲፕሊን፣ እርምጃን በተመለከተ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ኃላፊነት መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል፡፡

የህገ-መንግስቱን ድንጋጌ ተግባራዊ ለማድረግ በፌዴራልና በክልሎች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ተቋቁመዋል፡፡ ከፌዴራልና ከክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጆች መረዳት እንደሚቻለው የጉባኤው አባሎች ቁጥር የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ በፌዴራል ዘጠኝ፣ በትግራይ 17፣ በኦሮሚያ 9፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 11፣ በጋምቤላ 16፣ በአማራ(የክልል ጉባኤ) 12 ናቸው፡፡ የጉባኤው አባሎች ሰብጥርም እንዲሁ ይለያያል፡፡ በፌዴራል የጉባኤው አባሎች ከፍ/ቤትና ከተወካዮች ምክር ቤት፣ በትግራይ ከፍ/ቤት፣ ከሴቶች ማህበር፣ ከገበሬ ማህበር፣ ከፍትህ ቢሮ፣ ከጠበቆች ማህበር እና ከአስተዳደርና ፍትና ዘርፍ፣

ኦሮሚያ የክልል ጉባኤን በተመለከተ ከፍ/ቤትና ከምክር ቤት፣ ደቡብ ከፍ/ቤትና ከክልል ምክር ቤት ናቸው፡፡

የፌዴራልና የክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤም የዳኞች ምልመላ፣ ደመወዝ፣ ዲስፒሊን፣ ዕድገት፣ ዝውውር ፣ አበልና ህክምና የመወሰን ሥልጣን አሏቸው፡፡ በሌላ በኩል ዳኞች የመደልደል ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን መቅጠርና ማስተዳደር እና ሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎች የጠቅላይ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ሐላፊነት ነው፡፡ በየደረጀው በሚገኙ የፍ/ቤቶች ሐለፊዎች ይሔን ሥልጣን በውክልና ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ በፌደራልና በክልሎች ዳኞች የማስተዳደር ሐላፊነት a multi-branch responsibility ሞደል የተባለውን አስራር የተከተለ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ የፌዴራልና የክልሎች አስተዳደር ጉባኤ አባሎች ሲታይ ዳኞች በጉባኤው ውስጥ አብላጫውን ቁጥር አላቸው፡፡ የዳኝነት ነፃነትን ለማረጋገጥ በጉባኤው ውስጥ ዳኞች አብላጫውን ቁጥር መያዛቸው ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ዋናው ቁም ነገር የፌዴራልም ሆነ የክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤዎች ምን ያህል በተግባር ሐላፊነታቸውን በግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ እያከናወኑ ነው የሚለው ነው፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የፌደራል ፍ/ቤቶችና በክልል ፍ/ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጆች መሰረት የጉባኤው ሰብሳቢ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዜዳንቶች ሲሆን ምክትል ፕሬዜዳንቶች ደግሞ የጉባኤው አባል ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከፍ/ቤት የሚወከለ ዳኞች እንዴትና በማን እንደሚሰየሙ በአዋጆቹ ተመልክቷል፡፡ ለምሳሌ በፌዴራልና በጋምቤላ ክልል በጉባኤው ውስጥ አባል የሚሆኑ ዳኞች አሰያየም አገልግሎት ዘመንን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በትግራይና በአማራ ደግሞ ተወካዮቹ በዳኞች የሚመረጡ ናቸው፡፡ በኦሮሚያና በደቡብ ደግሞ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዜዳንቶች የሚሰየሙ ናቸው፡፡ የዳኝነት ነፃነትን ከማረጋገጥ አኳያ የትኛው አማራጭ የተሻለ ነው? ለምን?

2. በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ውስጥ ከፍ/ቤትና ከመንግስት አካላት ውጪ ሌሎች የሕብረተሰቡ ክፍሎች እንዲሳተፉ ማድረግ ጠቀሜታው ምንድን ነው?
3. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞን በማስተዳደር በኩል ፍ/ቤቶች ምን ያህል ከአስፈፃሚው አካል ተፅእኖ ውጪ ናቸው? ያለው ልምድ ከሕጉ ጋር ይጣጣማል? በተግባር ያለው ችግር ምንድነው?

1.4.3.2. የበጀት ነፃነት

አንድ አለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት ዝቅተኛ መመዘኛ ፍ/ቤቶችን በፍትህ አስተዳደር ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ በቂ በጀት ሊመደብላቸው ይገባል። የፍ/ቤቶች በጀት አግባብነት ካለው አካል ጋር በመቀናጀት ሊዘጋጅ ይገባል። በዚህ ውስጥ ፍ/ቤቶች ተገቢውን ተሳትፎ ማድረግና በጀቱም ሲፈቀድ የማስተዳደር ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል።

የበጀት ነፃነትን በተመለከተ የሐገሮች ልምድ የተለያየ ነው። ለምሳሌ፦ አሜሪካ፣ ሕንድና ጃፓንን ብንወስድ ፍ/ቤቶቹ የራሳቸውን በጀት ግምት አዘጋጅተው ለሕግ አውጪው በቀጥታ ያቀርባሉ። ሲፈቀድም የተፈቀደላቸውን በጀት ካለ አስፈጻሚ አካል ጣልቃ ገብነት የማስተዳደር ነፃነት አላቸው። በአሜሪካ የፍ/ቤቱን ባጀት ካለአስፈፃሚ አካል ጣልቃ ገብነት አዘጋጅቶ ማቅረብ የተቋማዊ ነፃነት መሰረታዊ ገፅታና ሕገመንግስቱ ካስቀመጠው የስልጣን ክፍፍል የሚመነጭ ነው። ይሄን አንድ አሜሪካዊ ዳኛ፦

> *"…. It is in conflict with the division of power which the constitution contemplates to allow the executive department to formulate the budget for the judiciary"* ***በማለት ከገለፀው መረዳት ይቻላል።***

የጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ኒዘርላንድ፣ ብራዚል፣ ደቡብ አፍሪካና የካናዳ ልምድ ደግሞ ከአሜሪካ፣ ሕንድና ጃፓን ተቃራኒ ነው። በእነዚህ ሐገሮች ፍ/ቤቶች የራሳቸውን በጀት ቀጥታ ለሕግ አውጪው አካል አቅርበው የማጸደቅ ስልጣን የላቸውም። የፍ/ቤቶች በጀት ለህግ አውጪው የሚቀርበው በሕግ አስፈጻሚ በኩል ነው። በእንዚህ ሐገሮች የፀደቀውን በጀት በማስተዳደር በኩል አስፈጻሚ አካል ከፍተኛ ሚና አለው።

የበጀት ነፃነትን በተመለከተ የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ሕገ-መንግስት ግልጽ አቋም ወስዷል። የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌደራሉን መንግሥት የዳኝነት አካል የሚያስተዳድርበትን በጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል። ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል። የክልል ፍ/ቤቶች በጀትም በየክልሉ ምክር ቤቶች እንደሚመደብ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 79(6) እና (7) ሥር ተደንግጓል። የክልል መንግስታት ሕገ-መንግስትም ተመሳሳይ ድንጋጌዎችን ይዘዋል። በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የፌደራልና የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የፍ/ቤቶችን በጀት በማዘጋጀት ለሕግ አውጪው ማቅረብና ሲፀድቅም የማስተዳደር ነጻነት አላቸው። ስለዚህ የፍ/ቤቶችን በጀት ማዘጋጀትም ሆነ ማስተዳደር ከአስፈጻሚው አካል ጣልቃ ገብነት ውጪ ነው። በጀታዊ ነፃነት ሙሉ በሙሉ ሕገመንግስታዊ እውቅና ተሰጥቶታል።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በሕገመንግስቱ ጥበቃ የተደረገለትን የበጀት ነፃነት ተግባራዊ አፈጻጸም ምን ይመስላል?
2. በአንዳንድ ክልሎች (ለምሳሌ ኦሮሚያና አማራ) ከሕገመንግስቱ በኋላ በወጡ አዋጆችና ደንቦች የሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጀት ፍ/ቤትንም ጨምሮ የሚቀርበው በገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በኩል ነው። የበጀት አስተዳደርን በተመለከተ ይህ ቢሮ ሰፊ ሥልጣን አለው። እነዚህ ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም ያለው አሰራር ከሕገመንግስቱ አኳያ እንዴት ይታያሉ? በሕገመንግስቱ ጥበቃ የተደረገለትን የበጀት ነጻነት ተግባራዊ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት?

1.4.4. ምልመላና ሹመት

ባለትዳ ሐ ር የፍትሕ ጎ ራ ፔ በ ፖሼፔ ሥራ ተመታብው በሚሰሩ ሰዎኖ ጥራት ላቭ ባተመሠረተ ቭው። ለዚህ ተ ሞ ባምልመላው ሒተፔ ወሳኝ ነው። አትታ አሜሪካዊ ባሕ ሊቅ ቭሄት በማነ ጸር ት ፣ህ ብለዋል፡-

> *In the long run, there is no guarantee of justice except the personality of the judges. In turn, most discussion of the quality of the judiciary center on how judges are chosen.*

ኣኖ ቀጥተቑም ሆት ቀጎ ተቑ ጸልሆት ተብ፣ ተኽ ፣ ማ ባባፔ፣ ዋፔ፣ ማስወራራፔ ወቨም ኃልቃ ብትፔ ችኻ መሆት አለባ ው ስለተባለ ብኖ ባ ፖትፔ ችሟፔ ሊ ርም ሊረ ጎም አቨኖልም። ባ ሕዚህ ሁቴ ዎኖ መ ር ወቨም አለመ ር በ ቨት ትቱ ቑ ባስብ ና ታክመፔ ወቨም ጎ ትካሬ ባሚወሰት ቴው። አትታ ቑ ተ ቋ ትቱት ለሕ በኖ ጸላተረ ሕ ት ብኖ መሠረፔ አታር ሎ ባ ፖትፔ ሥራ ተ ባሩት በመወ ሙ ምክትቨፔ ሊቨ ጎ መው ባሚኖለውት ውተ ለመቋቋም ባሙቨ ባመትወስ ብር ፔ ጸሌለው ጸላቨ ለተጎ ቀሱፔ አሉ ዊ ሁቴ ዎኖ ባአትቱ ወቨም ባሁሉም ባርቨ ጸመሆት አቨልዎም። ባዚህ አቨትፔ ቑ ባ ፖትፔ ችሟፔ መርህ ባ ታ ባሚላ ው ባ ለልተፖትፔ፣ ባትሟፔ፣ ባአመዛዛፖትፔ ባተዊርትፔ ባህሪ ሊ ረው አቨኖልም።

በቂ ባሕ ውቀፔ ቨላ ው፣ በኸበቨ ው ባተመሰ ት፣ ተዊር፣ ሰብአዊትፔ ባሚሰማ ው ሰዎኖ በዎርታ ሥራ ሒተፔ ለልተቑ በመሆት ባሕ ባበላቨትፔት ቨጸብራሉ። ቨስጸብራሉም። ባዎርታ ቤፔት ችሟፔ አሳልወው አቨሰጎም። ባዎርታ ቤፔት ክብር ባማስጎበቅ ብቃፔ ቨ ራ ዋል። ሕዝብ መት ስፔ በዎ/ቤፔ ላቨ ምትፔ ት ረ ራ ው ቨተር ሉ። ባምልመላ ሂተፔም ባዚህ አቨትፔ ብቃፔ ሊ ራ ው ባሚኖል ሰዎኖት ለሹመፔ ባሚቨበቃ መሆት አለበፔ። ለዚህም ባ ኣኖ ምልመላ ትቲፔ ቨካሄታ ባሚለው ባምልመላው መስወረ ኖ ምት መሆት አለባ ው ባሚለው በዓለም አቀዎ ተረ ጸዎተቑ ፔጹረፔ ቨ ገፑ ቨ ቴው።

ትተ ባተባበሩፔ መት ስ ፔ ባዎ/ቤፔ ችሟፔ መሠረ ዊ መርሆኖ ለ ፖትፔ ሥራ ባሚመለመሉ ሰዎኖ ባተሚላ ስብ ፣ ኖሎ ባሕ ሙቨ ወቨም ተ ቢ ባሕ ስልጎ ቨላ ው መሆት አለባ ው። ትተ ዓለም አቀዎ ባ ፖትፔ ችሟፔ ዝቅተቑ መመዘቑ ባ ቑኖ ባምልመላ ሂተፔ ለልተቑና ምልመላውም ተ ባ መስወር ኖ ላቨ ባተመሠረተ መሆት አለበፔ። በምልመላው ሂተፔ ባተመልማብ ባዝለቲጸ አመለካጸፔ ወቨም ለ ቋ ው ዝርቲ ቨለው ማፖትፔ ጸ ምፔ ውስጎ መ ባፔ ባለበፔም።

ምልመላት በተመለጸተ ወጎ ባሆት አሠራር ባለም። ባምልመላው ሂተፔ ጸሃ ር ሃ ር ቨበለቨቨል። አት ትታ ሃ ሮኖ ለ ፖትፔ ሹመፔ ባሚቨበቁ መስወር ኖት በ ልኮ ቨስቀምኃሉ። ለዚህም ባኮመት ሎው ስርዓፔ ተጸ ቨ ጸሆቑፔ አ ሮኖ ውስጎ ጸ ፡ ት ሊዝ ተብብ አዎሪካት መ ለኮ ቨኖላል። ለ ፖትፔ ሹመፔ ባሚቨበቁ

መስወር ኖት ከማስቀመጎ በተ ማሪ ጸ ትፔ ባሚቨ ቱ መስወር ኖት በዝርዝር ባሚቨስቀምጎ ሃ ሮኖም አሉ። ለምሣሌ በጸ ባአልኮል ሱስ ወቨም ባሥፔሕ ብሄር ወቨም ባወት ል ክስ ቨለበፔ ወቨም ባወሲብ ጎ ቃፔ አቤቱ ወቨም ባ ፂሲገዚት አቤቱ ቨለበፔ ሰው በ ትፔ ሊቀርብ አቨኖልም።

በሌላ በጾል አት ትታ ሐ ሮኖ ለ ፖትፔ ባሚቨበቁ መስወር ኖት አቨስቀምጎም። ለምሳሌ ወረትሳቨት ብትወስታ አ ፂስ ባሕ ሙሩቃት ጸሕ ፔምህርፔ ቤ ኖ በውተ ጸተመለመሉ በኂላ ወተ ሥልጎ ት ፂ ቡ ይተረ ል። ስልጎ ውም ለሰላሳ አትታ ወራ ኖ ባሚቆቨ ሲሆት ሥልጎ ውት በሚ ባ ቨጎ ቀቁ ሰልኃኣኖ በ ጎባኤ ወቨም በሥፔህ ሚኒስተር አቅራቢነት በሐ ራቱ ፕሬዜ ትፔ ቨሾማሉ። ቨህ ባወረትሳቨ ባምልመላ ሒተፔ ባ ለልተፖትፔት መስወርፔ ባሚቨሚላ ችው ብለው በምሳሌትፔ ባሚጎ ቅሱ ኼዘዋሥኖ አሉ።

በአሜሪካ ባወቲራል ሥ/ቤፔ ኣኖ በገዜዜ ትቱ አቅራቢትፔ በሴኔፔ ቨሾማሉ። ዕ ሥኖት አኃር ለፕሬዜ ትቱ ባሚቨቀርበው ባሴኔፔ አባሎኖ ያሱበት ኮሚቴ ችው። ቨህ ባምልመላ ሒተፔ ልኽትፔ በተጎ ቨቂትፔ መርህ ላቨ ባተመሠረተ ችው፡ ተብሎ ትተምሳሌ ቨጎ ቀሳል። በሌላ በጾል ተ ሞ በተለቨ ባጎ ቅላቨ ሥ/ቤፔ ኣኖት ሹመፔ በተመለጸተ ባምልመለው ሒተፔ ዝለቲካዊ ቨዘፔ ቨለው ችው ብለው ባሚተቷም አሉ።

በካ ወቲራል ኣኖ ባሚሾሙፔ በካቢኔው ችው። ዕ ሥኖ ተኃርተው ለካቢኔው ባሚቀርቡፔ በኮሚቴ ችው። ባኮሚቴው አባሎኖም ጾጎ በቆኖ ማህበር፡ ጸሥ/ቤፔ ጸሌሎኖ ህብረተሰቡ ክሥል ባተውኃጎ ው። ባኮሚቴው አባሎኖም ባሚሰባሙፔ በሥፔህ ሚኒስተር ሲሆት ኮሚቴውም አመልካዥኖት በተረ አውጎ ለካቢኔው ይቀርባል።

በአጎ ቃላቨ በምልመላ ሂተፔ ጸሐ ር ሐ ር ባተለቨባ ቢሆትም ምልመላ በዘወቀተ መጸ ወት ባለበፔም። ባምልመላው ሂተፔ መመዘኞ መሰወር ኖ ት ፂሁም ምልመላውት ለማካሄታ ሥልኃት ባተሰጎ ው አካል ምልመላውት ባሚካሔታብፔ አሠራር በ ልኽ መ ወቅ አለበፔ። ባምልመላው ሂተፔ ልኽትፔ ቨለው ጸሙስ ባኸ መሆት አለበፔ።

ወተ ሐ ራኖት ስትመለስ በኢ.ዉ.ታ.ሪ. ሕ መት ስፔ አትቀኮ 81 ሥር ትተተተት ው በወያኤራል ጎ ቅላቭ ዎ/ቤፔ ገዌዜ ትፔ ምክፔል ገዌዜ ትፔ በወተራል መት ሥፔ ጎ ቅላቭ ሚኚስፔር አቅራቢትፔ በሕዝብ ተወጸቦ ኖ ምክር ቤፔ ባሚሾሙ ሲሆት ባክልል ጎ ቅላቭ ዎ/ቤ ኖ ገዌዝ ትፔ ምክፔል ገዌዜ ትፔ ተ ሞ በክልሉ ርዕሰ መስተ ታር አቅራቢትፔ በክልሉ ምክር ቤፔ ቭሾማሉ፡፡ ባሌሎኖ ኣ ኖ ባምልመላ ሒተፔ ጸዚህ ባተለባ መሆት በወያኤራል በክልሎኖ መካጸለም መጎ ቹ ልብትፔ ቨለ መሆትት ጸዚሁ ከሕ መት ስፔቱ ድንጋጌ መረ ፔ ቭኖሳል፡፡

ቾ ሆ ለመስራፔ ባሚቨበቁ መመዘቾዎኖ በወተራል ኣ ኖ አስተ ተር ጎባኤ ማቋቋሚቨ አዋ በክልሎኖም በወጡ አዋ ኖ ውስጎ ተዘርዝረዋል፡፡ ዝኪህም፡-

1. ለወተራል ሕ መት ስፔ ማፖ መሆት በክልሎኖ ተ ሞ ለወተራል ለክልሉ ሕ መት ስፔ ማፖ መሆት
2. ባሕ ፔምህርፔ ውቨም በቂ ባሕ ልምታ
3. መልጸም ስም ኽክቨ
4. በወት ል ተጸሶ በዎ/ቤፔ ቨልተቀኃ
5. ዕታሜው ሃቨ አምስፔ ባሞላው /ኦሮሚቨ 21/
6. ባአዕምሮ በሸተቾ ቨልሆት/ ምቤላ ኦሮሚቨ/
7. በ ፖቾፔ ሙቨ ለመስራፔ ወቃተቾ ባሆት
8. ባክልሉ ሥራ ቋትቋ ጎ ትቅቆ ባሚቨውቅ /ኦሮሚቨ/ ው፡፡

ባመወቨቨ ጎ ቨቄዎኖ

1. ባወተራል ባክልል ጎ ቅላቭ ዎ/ቤ ኖ ገዌዜ ት ኖ ምክትል ገዌዜ ት ኖ ባምልመላ መስወርፔ ምትታትው?
2. ባምልመላ ሒተፔት በተመለጸተ በወተራል በክልሎኖ መካጸል ቨለው ተመሳሳቭትፔ ልብትፔ ምትታትው?
3. ባወተራል ዎ/ቤፔ ኣ ኖት ሹመፔ በተመለጸተ ባወተራል መት ስፔ ጎ ቅላቭ ሚኚስፔር ሥልኃ ት ምትታትው ?
4. ባ ኣ ኖ ምልመላ መመዘቾና ባ ፖቾፔ ችቾፔ መካጸል ቨለው ትባቶፔ ትቲፔ ቭ ለኻል?

5. ለወተራል ሕ መት ስፔ ማፖ ቨልሆት ሰው ቾ ሊሆት አቨኖልም። ለሕ መት ስፔ ማፖ መሆት ማለፔ ምት ማለፔ ነው? በምልመላ ሒተፔ ባሕ መት ስፔ ማፖቿፔ ትቲፔ ይመዘ ል?
6. ባሕ ልምታ ብኖ ቾ ሆ ለመሾም በቂ ነው? ቨሔ መስወርፔ ትቲፔ ቨ ቨል?
7. አት ትታ ሐ ሮኖ ጸሕ መ ቨ ው ሌሎኖ መስወር ኖ ጸ ምፔ ውስጎ ቨስ ባሉ። ለምሳሌ፡- ከጸ ት ሊዝ በምልመላው ሒደት ባዘር ባኸ አስተዋኳት ጸ ምፔ ውስጎ ቨስ ባሉ። ቨሔስ ጸ ቾ ሐ ር ሁቴ ር ትዴፔ ቨ ቨል? በተለይ በወደራል ባተለቨብ ብሔር ብሔረሰቦኖ በሚ ሩበፔ ክልል ለምሳሌ፡ ምቤላ፡ ቤትሻት ጎል ጎሙዝ ባተኩብ ብሔር ብሔረሰቦኖ ሕዝቦኖ ክልል አካቨ ትቲፔ ቨ ቨል? ያለው ልምድስ ምን ይመስላል? ከዳኝነት ነፃነት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድነው?
8. በኢ.ዉ.ታ.ሪ ሕ መት ስፔ በክልል መት ስ ፔ ሕ መት ስፔ በ ልኽ ትተተመለጸተው ጸን ቅላቨ ም/ቤፔ ገዬዜ ትፔ ምክፔል ገዬዜተትፔ በስተቀር ሌሎኖ ዳኣ ኖ በ ኣ ኖ አስተ ተር ጎባኤ አቅራቢቿፔ በክልል ምክር ቤፔ ቨሾማሉ። ጸዚህ ው ባሆት አሠራር ኢ-ሕ መት ስ ዊ ነው። በዚህ ረ ታ በክልሉ ቨለው ልምታ ምት ቨመስላል? የምልመላው ሒተፔ ምት ቨህል ልኽቿፔ አለው?

1.4.5 ባሥራ ዘመት ዋስፔ ጸሥራ መሰ በፔ ሥርዓፔ

ባ ፖቿፔ ቸቿፔ ጸማረ ጎ አካቨ ባሥራ ዘመት ዋስፔ (security and tenure) ወሳፖ ነው። ለልተቾ ባሆት ባምልመላ ሒተፔ በቂ ኖሎ ጎ ሩ ስብዕ ቨላ ውት ሰዎኖ ወተ ፖቿፔ ት ሩመን ቨተር ል። ባሥራ ዘመት ዋስፔ ተ ሞ በቂ ኖሎ ጎ ሩ ስብዕ ቨላ ው ሰዎኖ በ ፖቿፔ ሥራ ላቨ ት ሩቆብ ቨተር ል። በተ ማሪም አትታ ቾ ባሚሰን ው ውሳቴ በገቦለቲካ አካሉ ተቀባቨቿፔ አቨ ረውም ቨሆ ል በዚህ ምክንቨፔም ጸስራ ልባረር ኖሳለሁ ባሚል ፆራኖ በ ቾው አ ምሮ ት ቨቀረኽ ቾው ሥራውት ላለማኃፔ ወቨም ባስራ ጊዜውት ለማራዘም ሲል ጸህ ዉ ሊወሰት ባሚኖልበፔ ሁቴ ት ቨ ር ለመጸላጸል ባሥራ ዘመት ዋስፔ አቨንትቾ መሣሪቨ ነው።

ለዚህም ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት ባሕ ኀ በቃ እንዲደረግላት የዳኝነት ነፃነት መርህ ይጠይቃል። ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት በሕ አስወኛሚው አካል በ ሦ ዎቃታ ላቭ ባተመሠረተ መሆት ባለበፔም። ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት ዋስፔ ጸሌለው በሕ አስወኛሚው በ ሦ ዎቃታ ባሚወሰት ጸሆት ዳኞች በ ለልተፖቼ ውሳት ሊሰኑ አቭኖሉም።

ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት ዋስፔ ሊቭ ፖ ባሚኖለው ባ ኣ ኖት ሹመፔ ለሕቭወፔ ዘመት ወቭም ቾው በህ ባተወሰት ታማፔ ስጸሚተርስ ታረስ በማታረ ችወ። ቭሔ ብኖ በቂ አቭተለም። ባ ኣ ኖት ባሥራ ዘመት ዋስፔ ት ረው አትታን ዳኞ በሕ ባተወሰነው ባሥራ ዘመት ጸመታረሱ በዋፔ ባ ፖቼፔ ሥራ ሊቭስትሱፔ ባሚኖሉ ምክንቭ ኖ በ ልኽ በሕ ተተት ው መቀመጎ አለባ ው። በሕ ባተወሰችው ባሥራ ዘመት ጸመታረሱ በዋፔ ብቃፔ ባሥችም ባር ኖ ር ቭለባ ውት ኣ ኖ ጸሥራ ማሰ በፔ ወቭም ባሥራ ዘመ ው ት ቋረጎ ማታረ ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት ዋስፔ እት ረው ጸማታረ ር ባሚ አቭተለም።

ባሥራ ዘመት ዋስፔ በተባበሩፔ መት ስ ፔ ባዎ/ቤፔ መሠረ ዊ መርሆኖ አትቀኮ 11፣ 12 18 ሥር በ ልኽ ተተት ቿል። ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት ዋስፔ አስወላ ቼፔ ላቭ ምትም ክርክር ባለም። ብዙ ሐ ሮኖ ባ ኣ ኖት ሥራ ዘመት ባሕ ኀ በቃ አታር ዋል። ብራዚል፣ ኮለምቢቭ፣ ፕሊ፣ ፔሩ፣ አር ትቲና እና አሜሪጸ /ወቲራል ኣ ኖ/ ለምሳሌ ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት ስጸ ታማፔ ልክ ወቭም ለሕቭወፔ ዘመት ችወ። ሕትታ፣ ወረትሳቭ፣ ርመት፣ ካ ፣ ይጀሪቨት ተ ሞ ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት በሕ ባተወሰት ባጎረ መው ዕታማፔ ታረስ ችወ። ቭህ በሕ ባተወሰችው ባሥራ ዘመን ከመድረሱ በፊት አንድ ዳኛ ከሥራ ሊሰ በፔ ባሚኖልበፔ ምክንቭ ኖም ተቀምጎዋል። አትታት ቾ ባሥራ ዘመት ጸመታረሱ በዋፔ ጸሥራ ባሚሰ በትበፔ ሥርዓፔም ት ሁ ጸሐ ር ሐ ር ቭለቨቭል።

ትተ ዓለም አቀዎ ባ ፖቼፔ ችሻፔ ዝቅተቾ መመዘቾ ባዲሲፕሊት ጸሥራ ማሰ በፔ ሒተፔ ሚዘ ዊ መሆት አለበፔ። ቾው ባሚቀርብበፔት ክስ ባማወቅ ባመጸለጸል መብቱ ሊጎበቅለፔ ቭ ባል። ማትቾውም ባ ሲፕሊት ርም በሥት ም ባር ተትብ ወቭም በዎ/ቤቱ በ በሩ ተትቡኖ ላቭ ባተመሠረተ መሆት አለበፔ። በተ ማሪም በ ኣ ኖ ላቭ ባሚቀርብ ክስ በዎጎ ችፔ መታየት እንዳለበት የዳኝነት ነፃነት መርህ ይጠይቃል።

ባመወሸሸ ጎ ሸቁዎኖ

1. በሐ ራኖት ባ ኣ ኖ ባሥራ ዘመት ዋስፔ ት ረው ለማታረ ምት ምት ርም ዎኖ ተወስተዋል? ባ ኣ ኖት ባስራ ዘመት ዋስፔ ት ረው ለማታረ በወቲራል በክልል ተረ በቂ ባሕ ማዕቀዎ አለ? ሸለው ባሕ ማዕቀዎ ጸሌሎ ኖ ሐ ሮኖ ጸዓለም አቀዎ ባ ፖትፔ ትጭፔ ዝቅተቾ መመዘቾዎኖ ር ሲትሸር ምት ብመስላል?
2. ባወያሬራል ባክልል ጎ ቅላብ ዎ/ቤ ኖ ገፔዚ ት ኖ ምክፔል ገፔዜ ት ኖ ባሥራ ዘመት ዋስፔ ባሕ ጥበቃ ምን ይመስላል?
3. ባ ኣ ት ባሥራ ዘመት ዋስፔ ተ ባራዊ አወሻሸዎ በክልሎኖ ምት ብመስላል? ሸሉ ኖ ሮኖ ምትታ ው?

1.4.6. በቂ ክፍሸ

በቂ ክፍሸ ጸ ኣ ኖ ለሰባዊ ትጭፔ ር ተሸብዞ ባሚትላ ጉ ብ ትው። ባ ፖትፔት ሥራ በተ ቢው መት ታ ሊሸጸ ውት ባሚኖሉ ብቃፔ ሸላቸው ሰዎኖ ወተ ፖትቱ ለመሰብ ወብም ለማምኃፔ ት ሁም ብቃፔ ጎ ሩ ሥት ም ባር ሸላ ውት በ ፖትፔ ላብ ት ቆብ ለማታረ ባበቂ ክዎሸ መ ር አስወላ ትው። በተ ማሪም ተጸራጸሪ ወ ኖ በዎርታ አሰኃ ጎ ሒተፔ ላብ በ ኣ ኖ ላብ ሊሸሳታሩ ባሚኖሉፔት ባኢኮ ሚ ተዕ በመቀሸ ረ ታ በቂ ክወሸ ጎ ቀሜ አለው። ባላተ ሐ ሮኖ ዎ/ቤ ኖ ውስጎ ለተስዊዌው ሙስ አትታ ምክትሸፔ ለ ኣ ኖ ባሚጸወለው ክዎሸ በቂ አለመሆን ትተሆት ባሚ ልፁ ኸሐዋዎኖ አሉ።

ትተ ዓለም አቀዎ ባ ፖትፔ ትጭፔ ዝቅተቾ መመዘቾዎኖ ባ ፖትፔ ትጭፔት ለማረ ጎ ለ ኣ ኖ በቂ ክዎሸ ሊጸወላ ው ብ ባል። ባ ኣ ኖ ክፍያና ክዎሸውም መጠን ት ብቀሸ ባሕ ጎ በቃ ሊተረ ለፔ ብ ባል።

በአት ትታ ሐ ሮኖ ባ ኣ ኖ ተምወዝ ጸሌለው ባመት ስፔ ሠራተቾ ር ጹል ትው። ለምሳሌ ርመት፡ አት ትታ ሐ ሮኖ ተ ሞ ለ ኣ ኖ በቂ ክወሸ ሊጸወለ ው ትተሚ ባ በህ መት ስ ው ባሚደነግጉ አሉ። ለምሳሌ ጃፓንን መጥቀስ ይቻላል። በአንዳንድ ሐገሮች ደግሞ የዳኞች ክፍያ መጠን በህግ የተወሰነ ነው። እንዲሁም

የክፍያው መጠን እንደማይቀነስ ህገመንግስታዊ ጥበቃ ይደርጋለ፡፡ አሜሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ብራዚል፣ ሕንድና ጋናን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የዳኝነት ነጻነት ለማረጋገጥ የበቂ ክፍያ አስፈላጊነት ላይ ከሞላ ጎደል መግባባት ቢኖርም በቂ ክፍያ ምን መሆን አለበት ለሚለው ጥያቄ ግን ቁርጥ ያለ መልስ የለም፡፡ ሆኖም ግን ግላዊ ነፃነትን ለማረጋገጥ የዋጋ ግሽበትን ግምት ውስጥ በማስገባት የዳኞች ክፍያ በየጊዜው መታየት አለበት በሚለው ብዙዎቹ ይስማማሉ፡፡ ፕሮፌሰር ሺሞን ሼትሪት ይሔንኑ በማጠናከር የሚቀጥለውን ብሏል፡፡

> *Failure by proper organ of the state to take necessary action to increase judicial salaries and to account for price increase that constitutes an infringement to personal independence.*

የመወያያ ጥያቄ

በቂ ክፍያን በተመለከተ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ያለው የሕግ ጥበቃና በተግባር ያለውስ ልምድ ምን ይመስላል?

1.4.7. ዝውውርና እድገት

እንደ አለም አቀፍ የዳኝነት ነጻነት ዝቅተኛ መመዘኛ ዳኞች ከመደበኛው የዝውውር በስተቀር ከፈቃዳቸው ውጪ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መዛወር የለባቸውም፡፡ አንድ ዳኛ በዚህ መንገድ ብወስን በዚህ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ እዛወር ይሆናል የሚል ፍራች በእምሮው አንዳይቀረጽና ወደ ሌላ ቦታ ላለመዛወር ሲል ከሕግ ውጪ ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ እንዳይኖር የዳኞች ዝውውር በሕግ በግልጽ በተቀመጠ ምክንያት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

የዳኞች ዕድገት ደግሞ ተጨባጭ በሆኑ መመዘኛ በተለይ ችሎታ፣ ስብዕናና ልምድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ እድገት እንዴትና በምን መመዘኛ እንደሚሰጥ በህግ በግልጽ መቀመጥ እንዳለበት የዳኝነት ነፃነት መርህ ይጠይቃል፡፡

በአንዳንድ ሐገሮች የዳኞች ዕድገት አይታወቅም። ለምሳሌ ጀርመን፣ ሕንድ፣ ብራዚል፣ ደቡብ አፍሪካ፣ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ካናዳ ለሁሉም የፍ/ቤት እርከን ዳኛ የሚመደበው በሹመት ነው። በፈረንሳይ፣ ጋናና ጃፓን ደግሞ በእድገት ነው።

ወደ ሐገራችን ስንመለስ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኞች ዝውውርና የመወሰን ሥልጣን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ነው። ዝውውር በምን ምክንያትና በምን ጊዜ ውስጥ መፈጸም እንዳለበት የሚገልፅ ሕግ ግን የለም። በአማራ ክልል ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዝውውርን የሚመለከት መመሪያ ወጥቷል።

እድገትን በተመለከተም ግልጽ የሆነ መመዘኛ የለም። በአንዳንድ ክልሎች ለምሳሌ፡- ኦሮሚያ፣ ደቡብ፡ ሐረሪ እና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዳኞች የሥራ አፈፃፀም መለኪያ (performance evaluation) ተግባራዊ ለማድረግ አንዳንድ ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው።

በሌላ በኩል በፌዴራልና በክልል የዳኞችን ዕድገት የመወሰን ሥልጣን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ቢሆንም አንድ ዳኛ ከወረዳ ፍ/ቤት ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት ወይም ከከፍተኛ ፍ/ቤት ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለመምጣት የምክር ቤት ሹመት ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም ለሚለው ጥያቄ ተመሳሳይ መልስ የለም። ለምሳሌ በፌዴራል፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና በአማራ አንድ ዳኛ ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲድግ በክልሉ ምክር ቤት መሾም አለበት፡፤ በኦሮሚያ ደግሞ አንድን ዳኛ ከከፍተኛ ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ወይም ከወረዳ ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማሳደግ በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ ብቻ በቂ ነው። የትኛው አሠራር ከሕገመንግስቱ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሰልጣኞች ውይይት ሊያደርጉበት ይችላሉ።

ማጠቃለያ መወያያ ጥያቄዎች

1. በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገመንግስታዊ ሥርዓት ነፃና ፍትሐዊ የዳኝነት አካል ለመገንባት በቂ የሕግ ማዕቀፍ አለ? ያለው የሕግ ማዕቀፍ ከአለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት ዝቅተኛ መስፈርቶችና ከሌሎች ሐገሮች ልምድ ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

2. **ነፃና ፍትሐዊ የዳኝነት ሥርዓት በመገንባት ረገድ ያለው ዋነኛው ችግር ምንድ ነው? ያለውን ችግር ከዳኞች፡ ከመንግሥት ባለሥልጣናትና ከተከራካሪ ወገኖች አንፃር አንድ በአንድ ውይይት ይደረግበት፡፡ በዚህ ረገድ ከእናንተ ከሰልጣኞች ምን ይጠበቃል?**

ክፍል ሁለት

የዳኝነት ተጠያቂነትና ግልጽነት መርህ

መግቢያ

ፍ/ቤቶች ሕገ-መንግስታዊ ተልዕኮቻቸውን ለመወጣት የሚመሩባቸው ሌሎች መሰረታዊ መርሆችና በዚህ ክፍል የምንመለከታቸው የዳኝነት ተጠያቂነትና ግልጽነት ናቸው፡፡

ይህ ክፍል ሁለት ንዑስ ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል የዳኝነት ተጠያቂነትን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የዳኝነትን ተጠያቂነት ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ የተጠያቂነት ገፅታዎችና አይነቶች በጠቅላላው ይቀርባሉ፡፡ እንዲሁም በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ሥርዓተ መንግስት የዳኝነት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተዘረጉ ሥርዓቶች ምን ምን እንደሆኑ በዚሁ መጀመሪያ ንዑስ ክፍል የሚቀርቡ ናቸው፡፡ በሁለተኛው ንዑስ ክፍል የዳኝነት ግልጽነት መርህ በአጭሩ ይዳሰሳል፡፡

ሰልጣኞች ይህን ክፍል ሲያጠናቅቁ፡-

- የዳኝነት ተጠያቂነት ምንነት ያብራራሉ፡፡
- የዳኝነት ተጠያቂነት አስፈላጊነት ይገልፃሉ፡፡
- የዳኝነት ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ያሉ የተለያዩ አይነቶች ወይም ሞዴሎች አንድ በአንድ ይተነትናሉ፡፡
- በዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት መካከል ያለውን ትስስር ያስረዳሉ፡፡
- የዳኝነት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት በቂ የሕግ ማዕቀፍ መኖር አለመኖሩን መመዘን ይችላሉ፡፡
- የዳኝነት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እስከ አሁን የተወሰዱ እርምጃዎች ምን እንደሆኑ ይገነዘባሉ፡፡
- የዳኝነት ግልፅነት መርህ አስፈላጊነትና መርሁ በፍ/ቤቶች ተግባራዊ የሚሆንባቸውን መንገዶች ያብራራሉ፡፡
- በዲሞክራሳያዊ ሥርዓትና በዳኝነት ተጠያቂነት እንዲሁም በግልጽነት መርህ መካከል ያለውን ግንኙነት ማስረዳት ይችላሉ፡፡

2.1. የዳኝነት ተጠያቂነት

2.1.1. የዳኝነት ተጠያቂነት ምንነት

ለዳኝነት ተጠያቂነት ወጥ የሆነ ትርጉም የለም፡፡ የተለያዩ ፀሐፊዎች የዳኝነት ተጠያቂነትን በተለያየ መንገድ ለመግለጽ ሞክረዋል፡፡ ለምሳሌ ትተ **ሮጌሎ ፒሬዝ፣ ፔርዶሞ** የዳኝነት ተጠያቂነትማለት፡-

> *It is the consequence of individual judges wrongful acts or omission. Or it is control or supervision of judges to make certain that they do not deviate from the commonly accepted values of the public.*

ትተ **ሲዲማን** ደግሞ የዳኝነት ተጠያቂነት ማለት፡-

> *The responsibility of judges for their decision and/ or the liability of judges to give reasons or justification for their conduct in the resolution of dispute is not the product of mere whim or caprice.*

በእነዚህ ሁለት ትርጉሞች መሰረት የዳኝነት ተጠያቂነት ማለት አንድ ዳኛ ከሕግ ውጭ የፈፀመው ተግባር ወይም መፈፀም የሚገባውን ተግባር ባለመፈፀሙ ሊመጣ የሚችል ሐላፊነት ወይም ዳኛ በሕብረተሰቡ ተቀባይነት ካለው እሴት እንዳያፈነግጥ ወይም ውጪ እንዳይሰሩ የሚደረግ ቁጥጥር ወይም ክትትል ወይም ዳኛ ለሚሰጠው ውሳኔ ያለበት ኃላፊነት ማለት ነው፡፡

ዘመናዊው የዳኝነት ተጠያቂነተ ፅንሰ ሐሳብ ይዘት ለሦስት ጥያቄዎች መልስ መሥጠት መቻል አለበት፡፡ እነሱም አንደኛው የዳኝነት ተጠያቂነት ባለቤት (subject of judicial accountability) ማነው? ሁለተኛው የዳኝነት ተጠያቂነት ለማን? የሚለውና ሦስተኛው የዳኝነት ተጠያቂነት ባለቤት ወይም ባለቤቶች ተጠያቂ የሚሆኑት ምን ሲፈፅሙ ወይም ሳይፈፅሙ

ሲቀሩ ነው የሚሉት ናቸው፡፡ ስለዳኝነት ተጠያቂነት የሚሰጡ ትርጉሞችም ከዚሁ አኳያ ሊመዘኑ ይገባል፡፡

በቆየው አስተሳሰብ የዳኝነት ተጠያቂነት ባለቤት ተደርገው የሚወሰዱት ዳኞች ናቸው፡፡ በዘመናዊ የዳኝነት ተጠያቂነት ፅንስ ሐሳብ መሰረት ግን የዳኝነት ተጠያቂነት ባለቤት ዳኞች ብቻ ሳይሆን ፍ/ቤቶችንም እንደተቋም የሚያጠቃልል ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዳኞች ወይም የፍ/ቤቶች ተጠያቂነት ለሕግ አስፈጻሚ ወይም ለሕግ አውጪው ብቻ አይደለም፡፡ የዳኞች ወይም የፍ/ቤቶች ተጠያቂነት ለሁለቱም የመንግስት አካሎች፣ ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለዳኝነት አካሉ ለራሱ፣ ለሚዲያ ለinformal ቡድንና ለሌሎች አካላት ሊሆን ይችላል፡፡ ዳኞች ተጠያቂ የሚሆኑት አንድን ጉዳይ ሲወስኑ ለሚፈጽሙት ስህተት ወይም መፈፀም የሚገባቸውን ተግባር ሳይፈጽሙ ሲቀሩ ብቻ ሳይሆን ከችሎትና ከችሎት ውጪ ለሚያሳዩት ሥነ-ምግባርም ጭምር ነው፡፡ ፍ/ቤቶችም ዋናው ዓላማቸው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት በመሆኑ ለህብረተሰቡ ውጤታማ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ የመንግስትን ንብረት በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቶች እንደ ተቋም ለሚያከናውኑት ዳኝነታዊና አስተዳደራዊ ተግባሮች ተጠያቂነት አለባቸው፡፡

በአንድ ሐገር ለዳኝነት ተጠያቂነት የሚሰጠው ትርጉም የፖለቲካ አካላትና ሕዝቡ የፍትህ አስተዳደርን በተመለከተ በዳኛው ወይም በፍ/ቤቶች ላይ ያላቸውን አስተሳሰብ (attitude)፣ የሕግና የፖለቲካ ሥርዓት፣የዳኝነት ሥርዓትና ታሪክ ልምድ፣ በሐገሪቱ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡ ሰፋ ባለ መልኩ ግን የዳኝነት ተጠያቂነት ማለት፡- ዳኞችና ፍ/ቤቶች በሕግና በሥነምግባር ደንቦች መሰረት ለመሥራት ያለባቸው ኃላፊነትና በዚሁ መሰረት እንዲሰሩ ወይም መሥራታቸውን ለማረጋገጥ በሌሎች የሚደረግባቸው ተገቢ ቁጥጥርና ክትትል፣ ለሚፈፅሙት ተግባር ወይም ሳይፈጽሙ ለቀሩት ተግባሮች መጠየቅ ወይም ኃላፊ መሆን ወይም ምክንያት የመስጠት ኃላፊነት ወይም የፈጻሙት ስህተትና ሕገወጥ ተግባር የሚያስከትለውን ውጤት መሸከም ነው፡ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

2.1.2. የዳኝነት ተጠያቂነት ለምን?

ፍ/ቤቶች የሕዝብ ተቋማት ናቸው። በፍ/ቤቶች ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ ዳኞች በዳኝነት ሥልጣናቸው የተለያዩ ተግባራት ያከናውናሉ። የዳኝነት ሥልጣን ምንጭና መሰረት ደግሞ ሕዝብ ነው። በሌላ አነጋገር የዳኝነት ሥልጣን የሕዝብ ሥልጣን ነው። በዴሞክሲያዊ ስርዓት ደግሞ ሕዝቡ ሥልጣኑን የመቆጣጠር መብትም ግዴታም አለበት። ሥልጣን ደግሞ ካለተጠያቂነት ሊታሰብ አይችልም። ተጠያቂነት የሌለበት ሥልጣን ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጋር ሊጣጣም አይችልም።

የሕዝብ ተቋማት በሆኑት ፍ/ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ዳኞች የሕዝብና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ተግባራቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ። ሕግ ሊጥሱ ይችላሉ። የራሳቸውን የግል ፍላጎቶችና የፖለቲካ አስተሳሰብ ሊያራምዱ፣ አድሎ ሊፈፅሙ ይችላሉ። መሰና በውሳኔዎቻቸው ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ሊፈቅድ ይችላሉ። ሥራቸውን በቅልጥፍና ላይሰሩ ይችላሉ። በአጠቃላይ ዳኞች ሥራቸውን በሕጉ መሰረት ላይሰሩ ይችላሉ።

በአጭሩ የዳኝነት ሥራ ባህሪ ገለልተኝነት፣ አመዛዛኝነት፣ ሐቀኝነት፣ ታታሪነትና፣ ቅንነት፣ የሕዝብ አገልጋይነት ስሜትን የሚጠይቅ ነው። ዳኞች በዳኝነት ሥራቸው ይዜን ባህሪ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ከሌለ በስተቀር ዳኞች በተቃራኒው ወገንተኛና መሰኛ ሊሆኑ ይችላሉ።

ፍ/ቤቶችም እንደ ተቋም ሥራዎቻቸውን በቅልጥፍናና ውጤታማ በሆነ መልኩ ላከናውኑ ይችላሉ። በፍ/ቤቶች ውስጥ ያለ ደካማ አሰራርና ብቃት የሌለው አስተዳደር መኖር የፍትህ ጥራትን ሊጎዳው ይችላል። የሕዝብ ገንዘብና ንብረትን ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል።

እነዚህ ሁሉ ድክመቶች ለመቆጣጠርና ጥፋቶችን ለማረም የዳኝነት ተጠያቂነት አስፈላጊ ነው። ካለዳኝነት ተጠያቂነት የዳኝነት ነፃነት ሊረጋገጥ አይችልም።

የዳኝነት ተጠያቂነት ገፅታዎችና ዓይነቶች በአጠቃላይ

የዳኝነት ተጠያቂነት ሁለት ገጽታዎች አሉት፡፡ እነሱም ውስጣዊ ተጠያቂነት (Internal or endogenous) እና ውጫዊ ተጠያቂነት (external or exogenous accountability) ናቸው፡፡ ውስጣዊ ተጠያቂነት ዳኞችና ፍ/ቤቶች ለሕግና በዳኝነት ተቋሙ ውስጥ አግባብነት ላለው አካል ያለባቸውን ተጠያቂነት የሚመለከት ነው፡፡ ዳኞች የሚቀርብላቸውን ጉዳዮች በሕጉ መሰረት እልባት መስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በግልፅ ማከናወን አለባቸው፡፡ የዳኝነት ሥራ አካሔድ በማስረጃና በስነ ስርዓት ሕጎች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ በዳኝነት ስራ አካሔድ ውስጥ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ተከራካሪ ወገኖችን ያለ አድሎ በእኩልነት መስተናገድ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም በወንጀል ጉዳዮች ዳኞች የተከሳሾች ሥነ-ሥርዓታዊና ሕገመንግስታዊ መብቶች እንዳይጣሱ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

በእነዚህ የፍሬ ነገር ሕጎችና/substantive) የስነ-ሥርዓት ሕጎች መሰረት አለመስራት ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ በላይኛው የፍ/ቤት እርከን የሚገኙ ዳኞች በበታች ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ሊሽሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የውስጣዊ ተጠያቂነት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ውጫዊ ተጠያቂነት ዳኞችና ፍ/ቤቶች ለሚያከናውኑት ዳኝነታዊና አስተዳደራዊ ሥራ ወይም ተግባር ለመንግስት ፖለቲካ አካላት፣ ለሕዝብ፣ ለሚዲያና ለሌሎች አካላት ያለባቸውን ተጠያቂነት የሚመለከት ነው፡፡

ዳኞችና ፍ/ቤቶች ለተለያዩ አካላት ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የተጠያቂነታቸው መሰረትም የተለያየ ሊሆን እንደሚችል ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በዚህ ላይ በመመስረት የተለያዩ ፀሐፊዎች የዳኝነት ተጠያቂነት አይነቶችን በተለያዩ መደቦች ይከፋፍላሉ፡፡ ለምሳሌ **ሞሮ ካፒሊቲ** የዳኝነት ተጠያቂነትን በሦስት ሞዴሎች ይከፋፍላቸዋል፡፡ እነሱም፡-

1. Repressive /dependency/ model
2. Corporative autonomous (separateness/ model
3. Responsive /consumer-oriented/ model ናቸው፡፡ እንደ ካፒሊቲ በመጀመሪያው ሞዴል መሰረት ፍ/ቤት እና /ወይም ዳኞች ተጠያቂ የሚሆኑት ለመንግስት የፖለቲካ አካላት ሲሆን ሁለተኛው ሞዴል ደግሞ ከአንደኛው

ሞዴል በተቃራኒው ዳኞችና ፍ/ቤቶችን የመቆጣጠር ኃላፊነት ለፍ/ቤት ለራሱ የተተወ ነው። የሶስተኛው ሞዴል ደግሞ የፍ/ቤት እና/ ወይም ዳኞች ተጠያቂነት ከፖለቲካ አካላት ከፍ/ቤት እና ከሌላ ሕብረተሰብ ክፍሎች ለተውጣጣ አካል ነው። እንደ ካፒሊቲ ይሄ ሞዴል የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት ሚዛናቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ የሚያስችል ተመራጭነት ያለው ሞዴል ነው።

ወንዲል ኤል ግሪፌን የተባለው ፀሐፊ ደግሞ የፖለቲካ ተጠያቂነት፣ ውሳኔያዊ ተጠያቂነት (decisional accountability) እና የሥነምግባር (behavioral) ተጠያቂነት በማለት የዳኝነት ተጠያቂነትን በሦስት ይከፍላቸዋል። እንደ ግሪፌን የፖለቲካ ተጠያቂነት ምልመላ፣ የሥራ ዘመን ዋስትና እንዲሁም የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተ ዳኞች ለፖለቲካ አካላት ያለባቸውን ተጠያቂነት የሚመለከት ነው። በሌላ በኩል ውሳኔያዊ ተጠያቂነት ደግሞ ዳኞች ለሚሰጡት ትዕዛዝና ውሳኔ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው። የሥነምግባር ተጠያቂነት ደግሞ ለዲሲፕሊን ክስ መሰረት ለሆነው የዳኝነት ሥነምግባር ጋር የተያያዘ ነው።

ፕሮፌሰር ሺሞን ሼትሪት በራሱ በኩል የዳኝነት ተጠያቂነት በሦስት ከፍሎታል።
እነሱም፡-

1. የሕግ-ተጠያቂነት /legal accountability/
2. የሕዝብ ተጠያቂነት (public accountability)
3. ኢ-መደበኛ እና ማህበራዊ ቁጥጥር (Informal and social controls) ናቸው። እንደ ሼትሪት የሕግ ተጠያቂነት በዳኞች ላይ የሚደረግ ክትትል፣ የይግባኝ ሥርዓትን የፍትሐብሔርና የወንጀል ኃላፊነትን የሚያጠቃልል ነው። ሕዝባዊ ተጠያቂነት ደግሞ በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈጻሚው፣ በሚድያና በሌሎች ቡድኖች በዳኞች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር የሚመለከት ሲሆን ኢ-መደበኛ እና ማህበራዊ ቁጥጥር በሙያ አቻዎች አብረው ከሚሰሩ ሌሎች ዳኞች፣ የበላይ አለቆች የሚደረግ ቁጥጥርና ምክርን የሚመለከት ነው።

የመወያያ ጥያቄ

የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነትን ትስስር በተመለከተ ሁለቱም መርሆች የማይነጣጠሉና የማይጋጩ መርሆች ናቸው። ብዙ ፀሐፊዎች ይሄን ካሉ በኋላ ዋነው ግን በሁለቱ መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛን መጠበቅ ነው፡ ይላሉ። በዳኝነት ነጻነትና ተጠያቂነት መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛን እንዴት መጠበቅ ይችላል? በምሳሌ በማስደገፍ ውይይት ይደረግበት።

2.1.4. የዳኝነት ተጠያቂነት በኢ.ፌ.ድ.ሪ

2.1.4.1. መግቢያ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት ውስጥ ከተቀመጡት መሠረታዊ ሕገመንግስታዊ መርሆች ውስጥ አንድ ተጠያቂነት ነው። ተጠያቂነት የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ልዩ ባህሪ ነው። በሀገራችንም እየተገነባ ያለው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ካለተጠያቂነት ሊታሰበ አይችልም። የተጠያቂነት መርህም በሶስቱም የመንግስት አካሎች ተፈፃሚነት ያለውና ሊተገብሩት የሚገባቸው መርህ ነው። ስለዚህ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ነፃ የዳኝነት አካልን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን ነፃና ተጠያቂነት ያለበት የዳኝነት አካል የሚጠይቅ ነው። ተጠያቂነት የሌላው የዳኝነት አካል የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጠንቅ ከመሆን ውጪ የሚፈይደው ነገር የለም። ስለዚህ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ፍ/ቤቶች ያለባቸውን ሕገመንግስታዊ ተልእኮቸውን ለመወጣት ነፃ ብቻ ሳይሆኑ ተጠያቂም መሆን አለባቸው።

በኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግሥት የዳኝነት ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ሥርዓቶች ተዘርግተዋል። የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች በመሆናቸው የፌዴራልና የክልል ፍ/ቤቶችና ዳኞች ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ነው። በፌዴራልና በክልል ሕገመንግስቶች ውስጥ የዳኝነት ነፃነት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ሁሉ የዳኝነት ተጠያቂነት ገፅታ ወይም ይዘት አሏቸው ። ስለዚህ በኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት የዳኝነት ነፃነት ለማረጋገጥ የተዘረጉ ሥርዓቶች ሁሉ የዳኝነት ተጠያቂነትን የሚመለከቱ ናቸው። እነዚህ ሥርዓቶች የተለያየ ገፅታ ሊኖራቸው ይችላል። የዳኝነት ተጠያቂነት ገፅታዎች ውስጣዊና ውጫዊ ብለን

ለመከፋፈል እንችላለን፣፡ የበለጠ ደግሞ የፕሮፌሰር ሺሞን ሼቲሪት የአመዳደብ ስልት ላይ በመመስረት በኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት የዳኝነት ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ያሉ ሥርዓቶችን የሕዝብ ተጠያቂነት፣ የሕግ ተጠያቂነት፣ ኢመደበኛና ማህበራዊ ቁጥጥር በማለት ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሕዝብ ተጠያቂነት ፍ/ቤቶችና ዳኞች ለሌሎች የመንግሥት አካላትና ለፓሬስ ተጠያቂ የሚሆኑበትን፣ የሕግ ተጠያቂነት ደግሞ የይግባኝ ሥርዓት፣ የወንጀልና የዲሲፕሊን ተጠያቂነት የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው ፍ/ቤቶችና ዳኞች ለሕግ አውጪው ያለባቸው ተጠያቂነት፣ የዳኞች የወንጀልና የዲሲፕሊን ተጠያቂነት ብቻ ይሆናል፡፡ ሌሎቹ ሰልጣኞች በውይይት የሚያደርጉበትና ግማሾቹን ደግሞ ከግልፅነት መርህ ጋር የምናያቸው ይሆናል፡፡

2.1.4.2. ፍ/ቤቶችና ዳኞች ለሕግ አውጪው ያለባቸው ተጠያቂነት

የሕዝብ ተጠያቂነት ፍ/ቤቶች የሕዝብ ተቋማት ከመሆናቸው የሚመነጭ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትና በክልል ደግሞ በሶስቱም እርከን የሚገኙ ፍ/ቤቶች በቀጥታ በሕገመንግስቱ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ በሕገመንግሥቱም ሆነ በሌላ ሕግ የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች ዋና አላማ ሕጎችን በትክክል በመቶርጎም የሕዝብን መብቶች ፍላጎት ሚሟላት ነው፡፡

በሌላ በኩል በሕገመንግሥቱ የሉአላዊነት ስልጣን ባለቤት ሕዝቡ በመሆኑ በሕገመንግሥቱ ወይም በሌላ ሕግ የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች ሕጉን በትክክል በመቶርጎም የሕዝቡን መብትና ፍላጎቱን በትክክል እያሟሉ መሆኑን ሕዝቡ የማረጋገጥ የመቆጣጠር መብትና ግዴታ አለበት፡፡ በፍ/ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ዳኞች የዳኝነት ሥልጣን የሕዝብ ሥልጣን ነው፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቶችና ዳኞች ለሚያከናውኑት ሥራ ሁሉ ለሕዝብ ተጠያቂነት አለባቸው፡፡

ሕዝቡ የሉአላዊነት ሥልጣኑን ተግባራዊ ከሚያደርግበት መንገድ አንዱ በተወካዮች አማካኝነት ነው፡፡ የፍ/ቤቶችና የዳኞች የሕዝብ ተጠያቂነት ባሚረ ጎ ው በሕግ አውጪው በጾል ነው፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቶችና ዳኞች ለሕግ አውጪው በቀጎ ተጠያቂነት

አለባቸው፡፡ ሽህም ፍ/ቤቶችና ዳኞች ለሕግ አውጪው ያለባቸው ተጠያቂነት በተለያየ መንገድ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡

አንደኛው ሹመትና ከሥራ መሰናበት ነው፡፡ በክፍል አንድ እንደተጠቀሰው የፌዴራል ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በፌዴራል መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስቴር አቅራቢነት በተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ ሲሆን የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልል ርዕስ መስተዳድር አቅራቢያነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡ ከሥራ መሰናበትም ከዚሁ አንፃር የሚታይ ነው፡፡ ይህ የፌዴራልና የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንት ለሕግ አውጪው ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው፡፡ የሌሎች የፌዴራልና የክልል ፍ/ቤቶች ዳኞች ሹመትና ከሥራ መሰናበት ሂደት የሚያመላክተው እያንዳንዱ የፌዴራል ፍ/ቤት ዳኛ ለተወካዮች ምክር ቤት፣ የክልል ፍ/ቤት ዳኛ ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠያቂነት እንዳለበት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለዚህ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራል ፍ/ቤት ዳኞችን ሥነምግባር፣ የክልል ምክር ቤቶች ደግሞ የየክልሎቻቸውን ዳኞች ሥነ ምግባር ይቆጣጠራሉ፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ለተወካዮች ምክር ቤት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶች ደግሞ ለየክልል ምክር ቤቶቻቸው የፍ/ቤቶችን ሥራ ክንውን ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡ በሚቀርበው ሪፖርት በመንተራስ ሕግ አውጪው አካል የፍ/ቤቶችን ሥራ እንቅስቃሴ ይገመግማል፡፡ አስፈላጊው እርምትና እርምጃዎችን ይወስዳል ወይም እንዲወስድ ያደርጋል፡፡ ይሄ ሌላው የፍ/ቤቶችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የተዘረጋ ሥርዓት ነው፡፡

የፍ/ቤቶች በጀት የሚያፀድቀው በሕግ አውጪው አካል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራል ፍ/ቤት፣ የክልል ምክር ቤቶች ደግሞ የየክልሎቻቸው ፍ/ቤቶች በዕቅዳቸው መሠረት ማከናወናቸውን ለመቆጣጠር ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይሄ ፍ/ቤቶች ለሕግ አውጪው ያለባቸው ተጠያቂነት ተግባራዊ የሚሆንበት ሌላው መንገድ ነው፡፡

ሌላው የፍ/ቤቶችና የዳኞች ተጠያቂነት ተግባራዊ የሚሆንበት ዘዴ ሕገ አውጪው ሕግ ማውጣት ሥልጣን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሕግ አውጪው አካል የፍ/ቤቶችን

ሥልጣን የሚመለከቱ ሕጎችን በመሻር ወይም በመቀየር የፍ/ቤቶችን የሥራ እንቅስቃሴ ሊቆጣጠር ይችላል፡፡

2.1.4.3 የወንጀል ተጠያቂነት

የዳኝነት ነጻነት ዳኞችን ከወንጀል ሐላፊነት ነጻ አያደርጋቸውም፡፡ አንድ ዳኛ የወንጀል ሕግን ተላልፎ ከተገኘ እንደ ማንኛውም ሰው በወንጀል ይከሰሳል፡፡ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝም ተገቢው ቅጣት ይቀጣል፡፡ በወንጀል ሕግ መሠረት ዳኞች የመንግሥት ሠራተኞች በመሆናቸው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 402 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች በእነሱ ላይ ተፈፃሚነት አሏቸው፡፡ ዳኞች በሕግ አክባሪነታቸው በሕብረተሰቡ ውስጥ አሪያ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዳኞች ሥልጣናቸውን አለአግባብ መጠቀም የለባቸውም፡፡ ዳኞች የሕዝብ አገልጋይ እንጂ ተገልጋዮች አይደሉም፡፡ የዳኝነት ሥልጣንን ሕዝቡን ለማገልገል መጠቀም አለባቸው እንጂ ለግል ፍላጐትና ጥቅም ማራመጃ መጠቀም የሌለባቸው መሆኑን ላለፍታ እንኳን መዘንጋት የለባቸውም፡፡ የሄን በመዘንጋት ፍትህን በጥቅማ ጥቅም በመሸጥና በመለወጥ የዳኝነትን ሥራ ክብር የሚያዋርዱ ዳኞች ከሥራ መሰናበት ብቻ ሳይሆን በሕጉ አግባብ በወንጀል ሊጠየቁ ይገባል፡፡

በፌዴራልና በክልል (ለምሳሌ በኦሮሚያ) ጉቦ ሲቀበሉ እጂ ከፍንጁ ተይዘው በወንጀል ተከሰው የተፈረደባቸው ዳኞች አሉ፡፡ የሔም ዳኞችን የሕግ ተጠያቂነት ያለባቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

2.1.4.4. የዲሲፕሊን ተጠያቂነት

ከሕግ ውጪ የሚሰሩ ዳኞችን ለመቆጣጠርና ለመከታተል የዲሲፕሊን ተጠያቂነት አይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡ በክፍል አንድ እንደተመለከተው በዳኞች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ በሥነምግባር ደንብ ወይም በፍ/ቤቶች በዳበሩ ደንቦች (rules) ላይ መመሥረት እንዳለበት የዳኝነት ነፃነት መርህ አጥብቆ ይጠይቃል፡፡

አንድ ዳኛ ባዳኝነት ሙቭ የሚኀይቀውን ሥነምግባር ካላሟላ የተጠያቂነት መርህ የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድበት ወይም ከሥራው እንዲወገድ ይጠይቃል፡፡ የዲሲፕሊን ተጠያቂነት ተግባራዊ ለማድረግ ሥነምግባር ደንብ ከችሎት ውጭና

በችሎት ላይ የዳኞች ሥነምግባር ምን መሆን እንዳለበት የሚዘረዝርና ለዲሲፕሊን ክስ የሚያበቁ ድርጊቶችን በትክክል የሚያሰቀምጥ መሆን አለበት፡፡ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ተደራሽ የሆነና ግልፅነት ያለው የዲሲፕሊን አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓትና የሥነምግባር ጉድለት ሲፈፀም አስፈላጊውን እርምትና ቅጣት ሊወስድ የሚችል ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት የሚዘረጋው ሥርዓት በዳኛ በደል ደረሰብኝ የሚል ወገን አቤቱታውን በቀላሉ ለማቅረብ የሚያስችለው መሆን አለበት፡፡ ግልፅነት በተመለከተ የሚዘረጋው ሥርዓት አቤቱታ አቅራቢው የአቤቱታውን ውጤት ማወቅ የሚመስችለው መሆን አለበት፡፡

በተጨማሪም ሚዛናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታም የሆነ የዲሲፕሊን ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ በዳኛ ላይ የሚቀርብ የዲሲፕሊን ክስ በፍጥነት ወይም ባጭር ጊዜና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መታየት አለበት፡፡ የዲሲፕሊን ሥርዓቱ ክስ የቀረበበትን ዳኛ በተከሰሰበትን ጉዳይ መልስ መስጠትና የመከላከል መብቱን የሚከለክል ወይም የሚያጠብ መሆን የለበትም፡፡ የሚዘረጋው ሥርዓት በመጥፎ ልቦና በመነሳሳት በዳኛ ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ አቤቱታዎች ወይም የይግባኝ ጉዳዮችን እውነታነት ካላቸው አቤቱታዎች ከጅምሩ መለየት የሚቸስችል መሆን አለበት፡፡

በኢ.ፌ.ድ.ሪ. የዳኞችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ከተዘረጉት ሥርዓቶች ውስጥ የዲሲፕሊን ሥርዓት አንዱ ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ የሕገመንግስቱ አንቀጽ 79(4) (ሀ) እና 81(6) ማየቱ ብቻ በቂ ነው፡፡ ሕገመንግስቱ ከመጀመሪያውኑ ከዳኝነት ነፃነት መርህ ጋር በተጣጣመ መልኩ በዳኞች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ባመውሰድ ሥልጣን የዳኝነት አካል ትርጉም ባለው ሁኔታ ተሰታፊ ለሆነበት አካል መስጠት እንዳለበት በማመን ሥልጣኑ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የዳኞች ሥነምግባር ደንብም ማውጣት ሥልጣን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በፌዴራልና በክልል የዳኞች ሥነምግባርና የዲሲፕሊን ደንብ ወጥተው ተግባራዊ እየሆኑ ነው፡፡

እነዚህ በፌዴራልና በክልሎች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የወጡ የዳኞች ሥነምግባር ደንቦች ከተወሰኑ ልዩነቶች በስተቀር ተመሳሳይነት አሏቸው፡፡ ከሚታት ልዩነቶች ውስጥ አንዱን ለመጥቀስ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ፍ/ቤቶች ክልል ፍ/ቤቶች የዳኞች ሥነምግባር ዳኞች ጾናሎፔ ው በናሎፔ ላቭ ሊመሩባቸው የሚገባቸውን የስነ ምግባር መርሆች (guiding principles) አላከተተም፡፡ በደንቡ ውስጥ ተካተው የሚገኙት የዲሲፕሊን ጥፋቶች ብቻ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ፍ/ቤቶች ዳኞች ስነምግባር ደንብና ከክልል ደግሞ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፍ/ቤት ዳኞች ሥነምግባር ደንብ ብንመለከት ሁለቱም የሥነምግባር መርሆችና የዲሲፕሊን ጥፋቶችን በዝርዝር አካተው ይዘዋል፡፡ ሐቀኝነት፣ ታማኝነት፣ ግልፅነት፣ ቅንነት፣ የሕዝብ አገልጋይነት፣ ገለልተኝነት ሕግን ማክበር በደንቦቹ ውስጥ ከተካተቱት መርሆች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ መርሆች በማንኛውም ዳኛ ሊከበሩና ሊተገበሩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ስመርሆቹ ዝርዝር ስልጣኞች በሌላ ክፍለ ትምህርት የሚማሩት ይሆናል፡፡

በመጨረሻም ፍ/ቤቶችና ዳኞኖ የሕዝብ የመንግስትን አመኔታ ሊያተርፉ የሚችሉት የዲፕሊንን ሥርዓት ጨምሮ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ከሌላ የመንግስት አካል ጣልቃ ገብነት በራሳቸው የራሳቸውን የውስጥ ብልሹ አሰራርና የስነምግባር ችግር መቆጣጠርና ማስተካከል ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሌላ የመንግስት አካል ተፅኖ ስር መውደቃቸው አይቀርም፡፡ ለዚህ የጓቲማላና የፒሩን ፍ/ቤት የ ጠማቸውን ሁኔታ በምሳሌነት መጥቀስ ይችላል፡፡ በጓቲማላ (1993) የሙስና መስፋፋትና ከቁጥጥር ውጪ መውጣት ፍ/ቤቶች እንዲፈርሱ አድርጓል፡፡ በፒሩ (1992) በሙስና ሰበብ አስፈፃሚ አካል ፍ/ቤቶችን እንዲቆጣጠር ሥልጣን አት ሰነው ስለተተረ ብዙ ዳኞች በአስወክሚው አካል ከሥራ ተባረዋል፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የፌዴራልና የክልል ፍ/ቤቶች ዳኞች ለሕግ አስፈፃሚ ተጠያቂነት አለባቸው?
2. የዳኝነት ተጠያቂነት በማረጋገጥ ረገድ የይግባኝ ሥርዓት ያለው ሚና ምንድንነው? ፍ/ቤቶች (ፌዴራልና ክልል) በፌዴራል ጠቅይላ/ቭ ፍ/ቤት ሰበር ፓናል ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ (የቀደምትነት ውሳኔ) የመከተል ተጠያቂነት አለባቸው?
3. በዳኝነት ሥራ ውስጥ ያለን ሙስና ማግኘት ቀላል አይደለም፡፡ የሙስና ቀዳዳ ከተቻለ መዝጋት ካልተቻለ ደግሞ ለማጥበብ ከዲሲፕሊን ሥርዓት ውጭ ሌሎች ሊዘረጉ የሚገባቸው ሥርዓቶች ምን መሆን አለባቸው? ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዳኞች በሕጉ መሰረት እንዲሰሩ የዲሲፕሊን ተጠያቂነት ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ ነገር ግን የዲሲፕሊን እርምጃ የተፈፀመ ስህተትን ለማረም የሚወስድ እርምጃ ነው፡፡ ዳኞች በሕ ጉ እንዲሰሩ ሌሎች ሊወስዱ የሚገባቸው እርም ዎች ምን መሆን አለባቸው? ዳኞች በሕጉ መሰረት እንዲሰሩ አሁን እየተሰጠ ያለው ስልጠና ምን አስተዋፅኦ ይኖረዎል?
4. የዳኝነት ተጠያቂነት ለማረጋገጥ በፌዴራልና በክልል በቂ የሕግ ማዕቀፍ አለ?ያለው የሕግ ማዕቀፍ ምን ይመስላል?

2.2. የዳኝነት ግልፅነት

ግልፅነት የተጠያቂነት መርህ አንድ መግለጫ በመሆኑ ብዙን ጊዜ ከተጠያቂነት መርህ ጋር የሚሄድ ሌላው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረታዊ መርህ ነው።

ቀደም ሲል ከዳኝነት ተጠያቂነት ጋር በማያያዝ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የፍ/ቤቶች ሥልጣን ሆነ በፍ/ቤቶች ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ ዳኞች ሥልጣን ምንጭ ሕዝቡ በመሆኑ ሕዝቡ ፍ/ቤቶችና ዳኞች የሚጠበቅባቸውን ተግባር እያከናወኑ መሆን አለመሆናቸውን የማረጋገጥ የመቆጣጠር መብት አለው።

ሕዝቡ በፍ/ቤቶች የሚከናወኑትን ተግባሮች፣ በዳኞች የሚሰጡትን ትዕዛዞችና ውሳኔዎች በማወቅ እያንዳንዱ ዳኛ ይህ ን በትክክል እየተረጎመ መሆን አለመሆኑን ሥራውን በቅልጥፍና እየፈፀመ መሆን አለመሆኑን ማየት መታዘብና ማጋገጥ እንዲችል ፍ/ቤቶችና ዳኞች ሥራዎቻቸውን የግልፅነት መርህን መሰረት አድርገው ማከናወን ሲችሉ ብቻ ነው።

የግልፅነት መርህ በፍ/ቤቶች በተለያየ መንገድ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። አንደኛውና ዋነኛው ግልፅ ችሎት ነው። በፌዴራልና በክልል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዎጆች ውስጥ በሕግ በሌላ አካኋት ካልተደነገገ በስተቀር ፍ/ቤቶች በግልፅ ችሎት እንዲያስችሉ በወቲራል በክልል ም/ቤ ኖ ማቋቋሚቨ አዋ ተተት ቻል። ለምሳሌ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 6/1988 አንቀጽ 18 እና የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 26 መጥቀስ ይችላል። ይህ ፍ/ቤቶች ሥራዎቻቸውን በግልፅነት መርህ መሰረት እንዲፈፅሙ ለማድረግ የተደነገገ ነው።

ፍ/ቤቶች በግልጽ ችሎት እንዲያስችሉ ማድረግ የህብረተሰቡ ክፍል በዳኞች የሚሰጡትን ውሳኔዎች ትዕዛዞች በሕጉ መሰረት መሆን አለመሆኑን የራሱን ግንዛቤ እንዲኖረው ያደርጋል። ግልፅ ችሎት ለፕሬስም ክፍት ስለሚሆን ሕዝቡ የተሟላ መረጃ እንዲኖረው ያደርጋል። በተ ማሪም የፍትህ ጥራትና የዳኞች ተጠያቂነትና ከማረጋገጥ አኳያ ግልፅ ችሎት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ባተመኖ ሁኔታ እስካለ ድረስ ማንኛውም ዳኛ የዳኝነት ተግባሩን በግልፅ ችሎት የማስቻል ግቲታ አለበት። ግልጽነት ማትቸውም ዳኛ

ሊመራበት ጸሚገባው የሥነምግባር መርሆች ውስጥ አንዱ መሆኑ በፌዴራልና በክልል ዳኞች የሥነምግባር ደንብ ውስጥ በግልጽ ተደንግጓል። ለምሳሌ ባወቲራል ም/ቤ ኖ ኣኖ ሥነም ባር ተትብ አትቀኮ 8 ባብብ ብሔር ብሔረሰቦኖ ሕዝቦኖ ክልል ም/ቤ ኖ ባ ኣኖ ሥነም ባር ባ ፈስዕ ሊት ተትብ አት ኮ 7 መጎ ቀስ ቭኖል። ይሔን መርህ ተግባራዊ አለማድረግም የዲሲፕሊን ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል በግልጽ ተመልክቷል። ስለዚህ ም/ቤ ኖ በሕ በተወሰነው መሠረፔ ስራምኖ ውት ለሕዝብ ልኮ በሆት አካኋት ማጸ ወት ቭ ርባ ዋል።

ሌላው የግልፅነት መርህ በፍ/ቤቶች ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ የዳኞች ውሳኔዎች ለሕዝቡ እንዲደርሱ በማድረግ ነው። የዳኞችን ውሳኔ ለሕዝቡ በተለያዩ መንገድ ት ፈርሱ ማታረ ይችላሉ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የፍትህ ጥራትና የዳኞች ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ አኳያ የዳኝነት ሥራ በግልፅ ችሎት እንዲከናወን ማድረግ ያለው ሚና እንዴት ይገለፃል? የግልጽነትን መርህ በፍ/ቤቶች በግልፅ ችሎት ተግባራዊ ለማድረግ ዋናው ችግር ምንድን?ነው
2. በክፍል አንድ እንደተመለከተው ዳኞ የዳኝነት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ በፕሬስ ሊደርስባቸው ከሚችል አለአግባብ ተፅእኖ ነፃ መሆን እንዳለባቸው የዳኝነት ነፃነት መርህ ይጠይቃል። በሌላ በኩል ሕዝቡ ስለ ፖሼ ሥራ መረጃ የማኘት መብት አለው። ለዚህ ደግሞ ፕሬስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በዳኝነት ነፃነትና በፕሬስ ነፃነት መካከል ያለውን ሚዛን እንዴት መጠበቅ ቭኖል።

ዋቢ ጽሑፎች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት

የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ከነማሻሻያው

የፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ

የፌዴራል ፍ/ቤቶች ዳኞች ሥነምግባር ደንብ

የክልል መንግስታት ሕገመንግስት ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆች፣ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጆች፣ ሥነምግባር ደንቦችና ሌሎች አዋጆች

መንበረ ፀሐይ ታደሰ. (1994). **የኢትዮጵያ ሕግና ፍትህ ገፅታዎች አዲስ አበባ**

ማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና አዲዮቪዥዋል መምሪያ. (1994). **በኢትዮጵያ የዴሞክራሲዊ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች አዲስ አበባ**

The Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Proclamation No.414/2004.

Alemayehu Tegene. (2007). Independence and Accountability of Oromia Regional State Judiciary In Light of The Judicial Reform Program. (Master Thesis AAU unpublished)

Canadian Judicial Council. (1998). Ethical Principles for Judges. Ottawa, Ontario: Canadian Council

Ministry of Capacity Building. (2002). Justice System Reform in Ethiopia: Proceeding of the Work Shop on Ethiopian's Justice Reform, Addis Ababa: MCB

Shetreet,Shimon, and Jules Deschens, (eds.,) (1985). Judicial Independence: The Contemporary Debate, Dordrecht: Martinus Nijhoff Publishers.or Martinus Nijhoff Publishers, Boston/Lancaster.

Shetreet, Shimon. (1994). Justice in Israel: A Study of the Israeli Judiciary. Dordrecht/Boston/ London: Martinus Nijhoff Publishers

Vanderbilt, Arthur T. (1952). Cases and other Materials on Modern Procedure and Judicial Administration. New York: Washington Square Publishing Corp

Cappelletti, M. (1983)."Who Watches the Watchmen? A Comparative Study on Judicial Responsibility." 31 American Journal of Comparative Law

Dakolias, Maria and Thachuk, Kim (2000). "Attacking Corruption in the Judiciary: A Critical Process in Judicial Reform." 18 Wisconsin International Law Journal

Griffen, Wendel L. (1998). "Comment: Judicial Accountability and Discipline." 61

Larkins, Christopher. (1996). "Judicial Independence and Democratization: A Theoretical and Conceptual Analysis". 44 American Journal of Comparative Law 4

Oxner, Sandra E (2003). "The Quality of Judges." The World Bank Legal Review: Law and Justice for Development Vol. 1 The Hague/London/New York: The World Bank

Rosenn, Keith S. (1987). "The Protection of Judicial Independence in Latin America." 19 International American Law Review 1

Seidman, Louis Michael (1987). "Ambivalence and Accountability." 61 Southern California Law Review

White, Penny J. (2002). "Judging Judges: Securing Judicial Independence by Use of Judicial Performance Evaluations." 29 Fordham Urban Law Journal

Perez Perdomo, R. Independence and Accountability.

International Bar Association Minimum Standards on Judicial Independence (1982)

United Nation Basic Principles on the Independence of the Judiciary (1985)

Universal Declaration on the Independence of Justice (1989)